# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 135 ጥር 15 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የዲጂታል ሥርዓት ለዘመኑ ኢኮኖሚ ልማት

ወርቅነሽ ደምሰው

**ዜና ትንታኔ**



ኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት የሚያስችላትን ዲጂታል 2025 ስትራቴጂ ቀርጻ ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች። ዲጂታል ኢትዮጵያ እውን በማድረጉ ሂደትም የኢኮኖሚ እድገቱን ለማፋጠን የሚረዱ ዲጂታል አሠራሮችን በመዘርጋት በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተተገበሩና እንዲስፋፉ እየተደረገ ነው። ለአብነትም ዲጂታል ባንኪንግ፣ ቴሌብርንና መሰል አገልግሎቶች የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ የዲጂታል አሠራሮች የኢኮኖሚን እድገት በእጅጉ እያፋጠኑ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ።

ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው ባለፉት ስድስት ወራት በዲጂታል የባንክ አገልግሎት አማራጮች ከሁለት ነጥብ 8 ትሪሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ዝውውር ተደርጓል። በቴሌ ብር አማካኝነት ደግሞ 3 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር በላይ ዝውውር መፈጸም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮ ቴሌኮም መረጃ ያመላክታል ።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ እድገት ለኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋጽኦ ምንድነው? ቴክኖሎጂውን በምን መልኩ ብንጠቀም ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ይሆናል ስንል የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች አነጋግረን ማብራሪያ ሰጥተውናል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ብርሃኑ ደኑ (ዶ/ር) ቴክኖሎጂ ሲባል በምጣኔ ሀብት እሳቤ የምርትና የአገልግሎት ግብዓቶችን የምንጠቀምባቸው ሁኔታዎች የሚገልጽ እንደሆነ ይናገራሉ። የሰው ጉልበት፣ ካፒታልና የተለያዩ ግብዓቶችን ብንጠቀም በምን ያህል መጠንና ሁኔታ ማምረትና አገልግሎት መስጠት ያስችላል የሚለውን የምናሰላበት ነው ይላሉ።

ለአብነትም ሲጠቅሱ ከአንድ ሄክታር መሬት ምን ብንጠቀም 100 ኩንታል ምርት ማምረት እንችላለን የሚለውን ለማስላት የሚያስችል እንደሆነ ያመላክታሉ።

ቴክኖሎጂ ስንል የሰው ልጅ ከምርምር ያገኘውን እውቀት ተጨባጭ በሆነ የማምረት አቅም ላይ ማዋል እንደሆነ ጠቅሰው፤ ማሽን ወይም የምናመርትበት መሳሪያ የቴክኖሎጂ እድገት ውጤት የሚባል ነው። ይህ መሳሪያ የሰውን ጉልበት

የዲጂታል ሥርዓት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል













አቶ ሰለሞን ሳሴ

## ቋሚ ኮሚቴው በአፈር ማዳበሪያ ስርጭት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራ አሳሰበ

- አራት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመስኖ ልማት እየተሰራጨ ነው

ገጽ 8

## “የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም ማስከበር ላይ ብሔራዊ መግባባት ሊኖር ይገባል”

- አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ



በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ በሕዝቦች የበላይነትና ተጠቃሚነት እንዲሁም ሀገራዊ ጥቅምን ማስከበር ላይ ብሔራዊ መግባባት እንዲሁም የጋራ አቋም ሊኖር ይገባል ሲሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ገለጹ።

አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ በብሔራዊ መግባባት ላይ ያተኮረው ሁለተኛው የፓርላማ የዜጎች መድረክ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ብሔራዊ መግባባት ለሀገር ሰላምና ብልፅግና ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ በሕዝቦች የበላይነትና ተጠቃሚነት እንዲሁም ሀገራዊ ጥቅምን ማስከበር ላይ ብሔራዊ መግባባት እንዲሁም የጋራ አቋም ሊኖር ይገባል።

ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ያሉን የአመለካከት ልዩነቶች ጤናማና ሕገ መንግሥታዊ መሆናቸውንም አመልክተው፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ በብሔራዊ ጥቅምና በሕዝብ ተጠቃሚነት ዙሪያ ብሔራዊ መግባባትና የጋራ አቋምን ማጠናከር እንደሚገባ ገልጸዋል።

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ልዩነታቸውን ወደ ጎን ትተው ኢትዮጵያን ከወረራ ጠብቀውና

«የኢትዮጵያን ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



# ሕፃናትን ከጉልበት ብዝበዛ ለመታደግ

ቤዛ እሸቱ

**ዜና ሀተታ**

ሕፃናት የሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ተሟልቶላቸው ከትምህርት ገበታ ሳይርቁ እንዲያድጉ ይፈለጋል። የሕፃንነት እድሜያቸው ስለመተዳደሪያቸው የሚያስቡበት ሳይሆን ከእኩዮቻቸው ጋር የሚቦርቁበት ሊሆን እንደሚገባ ብዙዎች ይስማማሉ። በሀገራችን ግን ከዚህ በተቃራኒ ሕፃናት ጎዳና ላይ ምጽዋት ከመጠየቅ አንስቶ ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የማኖር ኃላፊነት ተሸክመው ይታያሉ።

በየጎዳናው ሚዛን አጠገባቸው አስቀምጠው ተመዘኑ እያሉ የሚማጸኑ እና ሶፍትና ማስቲካ ይዘው ወጪ ወራጁ እንዲገዛቸው የሚለምኑ በርካቶች እንደሆኑ ይስተዋላል። በሕፃናቱ የሥራ ሥምሪት ዙሪያ ሕጉ ምን ይላል? ሕጉ የማይፈቅድ ከሆነስ ተግባሩን ለማስቆም ምን እየተሠራ ነው ስንል ባለሙያዎችን ጠይቀናል።

ሕፃናትን ጉዳት ላይ ከሚጥሉ ጉዳዮች አንዱ በተለያዩ ምክንያቶች ለብዝበዛ መዳረጋቸው ነው የሚሉት በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕፃናት መብት ስርጸትና ሰብእና ቀረጻ ዴስክ ኃላፊ አቶ በለጠ ዳኜ፤ ሕፃናት በመማሪያ እድሜያቸው መሰረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ መማር ሲገባቸው ሥራ ላይ እንዲሠማሩ ማድረግ ጉልበት ብዝበዛ ነው ይላሉ።

አቶ በለጠ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመከላከል እየሠራ ቢሆንም የሕግ ክፍተቶች መኖራቸው የታሰበውን ያህል ውጤት እንዳይመጣ አድርጓል ይላሉ።

ሕፃናት መሠረታዊ መብቶቻቸውንና ፍላጎታቸውን በማይጥስ መልኩ አቅማቸው በሚፈቅደው ልክ ቤተሰቦቻቸውን ማገዝ ይችላሉ የሚሉት የዴስክ ኃላፊው፤ ይሁንና ቤተሰቦቻቸውን ለማገዝ በሚሠሩት ሥራና በጉልበት ብዝበዛ መሃል ያለው ልዩነት በሕጉ በግልጽ አለመቀመጡን ይጠቅሳሉ። ይህን የሚደነግግ ሕግ ባለመኖሩ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛና ቤተሰብን ማገዝ የሚሉት አሻሚና አከራካሪ ጉዳዮች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ያም ቢሆን በየጎዳናው ሚዛን ይዘው ተመዘኑ የሚሉ ወይም እቃዎችን ግዙን እያሉ የሚለምኑ ሕፃናት፤ በትምህርት መዋያ ጊዜያቸው በማይመጥናቸው ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚታዩ በመሆናቸው እነዚህን መሰል ድርጊቶች የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥርና የሙያ ደህንነት ዴስክ ኃላፊ አቶ ጥኡመዝጊ በርሄ በበኩላቸው፤ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በሕብረተሰቡ ዘንድ ከሕፃናት ሥራ ጋር የማመሳሰል ሁኔታ እንዳለ ጠቅሰው፤ የሕፃናት ሥራና ጉልበት ብዝበዛ ግን የተለያዩ ናቸው ይለሉ።

እንደ አቶ ጥኡመዝጊ ማብራሪያ የሕፃናትሥራ በሕፃናት የሚሠራና ተቀባይነት ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ሆኖ የትምህርት ሁኔታ የማያስተጓጉል፣ የጤና ጉዳት የማያስከትል፣ የሕፃናትን የመልካም አስተዳደግ እንክብካቤ የማያደናቅፍ የሥራ አይነት ነው። ይህም በአብዛኛው በቤተሰብ ውስጥ የሚከናወንና ልጆቹ ምግባራቸው የታነጸ እንዲሆንና ሥራ እየለመዱ እንዲያድጉ የሚረዳ ነው።

በሀገራችን ዝቅተኛው የመሥሪያ እድሜ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 14 ዓመት እንደነበርና በቅርቡ ወደ 15 ዓመት ከፍ እንዳለም ይገልጻሉ። በዚህ መሰረት እድሜያቸው ከ15 ዓመት ጀምሮ ያሉ ሕፃናት ለእነሱ የማይፈቀዱ የሥራ አይነቶችን ትተው ሌሎቹን መሥራት እንደሚችሉና ከ15 ዓመት በታች ያሉት ግን ቤተሰብን ከማገዝ ውጭ ሥራ መሥራት እንደሌለባቸው ተናግረዋል።

ሕፃናት መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ በትምህርት ገበታቸው ላይ መገኘት አለባቸው የሚሉት አቶ በለጠ፤ ነገር ግን በአስገዳጅ ሁኔታ ሕፃናት መሥራት ካለባቸው ከ15 ዓመት ጀምሮ መሥራት የሚችሉት የሥራ ዝርዝር በአዋጅ መቀመጡን ጠቅሰዋል። በተለይም በኤሌክትሪክ፣ በማዕድንና መሰል አደጋ በሚያስከትሉ ሥራዎች ላይ መሳተፍ እንደሌለባቸው ተናግረዋል።

ነገር ግን አቅማቸው በፈቀደና ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ መሳተፍ ይችላሉ። የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የሚባለው የመማር ሁኔታን የሚገድብ፣ ለአደጋና ለጤንነት መስተጓጎል የሚዳርግ እንደሆነም አንስተዋል።

አቶ ጥኡመዝጊ በበኩላቸው፤ አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የሚባልም እንዳለ ይጠቅሳሉ። ይህ ሕፃናትን በባርነት ወይም ተመሳሳይ በሆነ መልክ አስገድዶ ማሠራት፣ ሕፃናትን ለውትድርና መቅጠር፣ መመልመልና በጦርነት እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ሕፃናትን ለወሲብና ወሲብ ቀስቃሽ ለሆኑ ትእይንቶች ማሰማራት፣ እጽ እንዲሸጡና እንዲያመርቱ ማድረግን ያካትታል ይላሉ።

በሀገራችን የሦስቱን ልዩነት ያለመረዳትና የሕፃናት ሥራን የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የማለት፤ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ደግሞ አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የማለት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመዋል። በመሆኑም በሀገራችን አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ አለመኖሩን ይናገራሉ። ያም ቢሆን ጦርነት ሲኖር ሊያጋጥም እንደሚችልና ከዚህ ውጪ ባሉት ጊዜያት ግን በመረጃ የተደረገፈ እዚህ ቦታ አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ አለ የሚል ተጨባጭ መረጃ አለመኖሩን ተናግረዋል። ነገር ግን በሀገራችን



በስፋት የሚታየው የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ እንደሆነም አስረድተዋል።

በተለይም በሸሮ ሜዳ አካባቢ ለሽመና ሥራ ፤ በገጠር ለእርሻ ሥራ ልጆች ከትምህርት ገበታቸው ተስተጓጉለው ሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሁኔታ አለ የሚሉት አቶ ጥኡመዝጊ፤ ለዚህም ዋናው ገፊ ምክንያት የቤተሰቡ ድህነት መሆኑን ተናግረዋል። ወላጆች ድህነቱ ሲገፋቸው ልጆች አስርም አምስትም ይዘው እንዲመጡ ወደ ሥራ ያሰማሯቸዋል ነው ያሉት።

ማህበረሰቡን በማስተማር ሕፃናቱን ከዚህ መጠበቅ እንደሚቻል ተናግረዋል። ለዚህም ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከክልል ቢሮዎች ጋር ለግንዛቤ ማስጨበጥ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ያስረዳሉ።

ሕፃናቱን ለጉልበት ብዝበዛ የሚዳርጋቸው ዋና ምክንያት ድህነት መሆኑን አቶ በለጠም ይስማማሉ። የቤተሰብ ድህነት ሲኖር ልጆች ከቤተሰብ ተለይተው በሌሎች አሳዳጊዎች እጅ የሚገቡበት ሁኔታ እንዳለና በተለይ በከተሞች አካባቢ ለጉልበት ብዝበዛ ሲዳረጉ እንደሚታይ ያስረዳሉ።

በርካታ ልጆች ወደ ከተማ በሚፈልሱባቸው አካባቢዎች በአካል በመሄድ ሥራ መሰራት መጀመሩን ተናግረዋል። ሕፃናት በተለያዩ ምክንያቶች ከትምህርት ገበታቸው ሲለዩ ከእኩዮቻቸው እኩል እንዲሆኑ የተለየ ስርዓተ ትምህርት (ካሪኩለም) በመቅረጽ ወደ ትምህርት ገበታቸው ተመልሰው ትምህርታቸውን እንዲማሩ የሚደረግበት አግባብ መኖሩንም ተናግረዋል።

በርካታ ሕፃናት በተለይም ከደቡብ ክልል ወደ ከተሞች የሚፈልሱ መሆኑን ተናግረው፤ በተለይም ዋነኛ ተቀባይ ከሆነው ከአዲስ አበባ አስተዳደር ጋር በመሆን ላኪ ወደ ሆኑት አካባቢዎች በመሄድ የተለያዩ ሥራዎች መሥራታቸውን ገልጸዋል። ለእንደዚህ አይነት ችግር የተጋለጡ ቤተሰቦችን የኢኮኖሚ አቅም በማጎልበት ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል።

አቶ ጥኡመዝጊ በበኩላቸው፤ ስለሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ለወላጆች ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሲሰጥ እንደነበር ተናግረው፤ ሕፃናትን ለሥራ የሚያሰማሩ ድርጅቶች በሕግ እንዲጠየቁ ይደረጋልም ብለዋል።

በመላ ሀገሪቱ ከ600 በላይ ተቆጣጣሪዎች እንዳሉ ጠቅሰው፤ ሕፃናት በድርጅቶች ውስጥ ሥራ አለመሰማራታቸውን ይቆጣጠራሉ ብለዋል። ያም ብቻ ሳይሆን እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው ከ15 እስከ 18 የእድሜ ክልል የሚገኙትም ቢሆኑ ከሚፈቀደው በላይ ሥራ እንዳይሠሩ ቁጥጥር እንደሚደረግ ገልጸዋል።

# ድጋፉ ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ የደም ባንክ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ነው

ሶሎሞን በየነ

አዲስ አበባ፡- ለክልል ደም ባንኮች የተደረገው የሕክምና መሳሪያዎች ድጋፍ ለኅብረተሰቡ ጥራቱን፣ ደህንነቱንና ደረጃውን የጠበቀ ወቅቱን የሚመጥን የደም ባንክ አገልግሎት ለመስጠት እንደሚያስችል የጤና ሚኒስቴር ገለጸ።

የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለ53 የክልል ደም ባንኮች 128 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የሕክምና መሳሪያዎችና ግብዓቶችን ትናንት ድጋፍ አድርጓል።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር መቅደስ ዳባ በድጋፉ ርክክብ መርሃ ግብሩ ላይ እንዳሉት፤ መንግሥት አዋጅ አውጥቶ፣ ፖሊሲ ቀርፆ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራቸው ሥራዎች ውስጥ አንዱና ግንባር ቀደሙ የደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ነው። ከዚህ አኳያ የክልል ደም ባንኮች ለኅብረተሰቡ ጥራቱን፣ ደህንነቱንና ደረጃውን የጠበቀ ወቅቱን የሚመጥን የደም ባንክ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ 128 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የሕክምና መሳሪያዎች ድጋፍ ተደርጎላቸዋል ብለዋል።

መንግሥት ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ግብዓቶችን ማሟላት ላይ በትኩረት እየሠራ ይገኛል ያሉት ሚኒስትሯ፤ የተደረገው ድጋፍ ጥራት ያለው የደም ባንክ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል ብለዋል።




ሚኒስትሯ ዶክተር መቅደስ፤ "አንዱ በትኩረት እየሠራንበት ያለው የምንሰጣቸው አገልግሎቶችን ወደ ኅብረተሰቡ ማስጠጋት ነው" ሲሉ ገልጸው፤ ድጋፍ የተደረጉት የሕክምና መሳሪያዎች ቴክኖሎጂው የደረሰበትና ዘመኑን የዋጀ የደም ባንክ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በቅርበት ለመስጠት የሚያስችሉ እንደሆነ አመላክተዋል።

በቅርቡ ኅብረተሰቡ ወደ ጤና ተቋሟት የሚመጣበት፣ ጤና ተቋማት ደግሞ ወደ ኅብረተሰቡ የሚደርሱበትን አቅም የሚጨምሩ የአምቡላንስና ሞተር ሳይክሎችን ለክልል ጤና ተቋማት ድጋፍ መደረጉን አውስተው፤ በጥራት የደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎቱን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ መሰል ድጋፎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

ደም መለገስ፤ የሚተካ ደምን ሰጥቶ የማይተካ ክቡር የሆነውን የሰውን ልጅ ሕይወት የሚያድን ተግባር ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ አሁንም በደም እጦት የሚሞቱ ብዙ እናቶችና ሕፃናት አሉ። ደም አስፈልጓት የምትሞት እናት እንዳትኖር ደም በመለገስ የሰውን ሕይወት በማዳን ከሚገኘው ደስታ ተቋዳሽ እንዲሆኑ ለኅብረተሰቡ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አሸናፊ ታዘበው በበኩላቸው፤ አገልግሎቱ ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በትብብር ከሚሠራው ሥራ ውስጥ አንደኛውና ወሳኙ ኃላፊነቱ የክልል ደም ባንኮችን አቅም መገንባት እንደሆነ ጠቁመው፤ ከዚህ አኳያ የተቋሙ የዘወትር ሥራ ከሆነው የደም የምርመራና አቅርቦት ሥራዎች እና ቴክኒካል ድጋፎች ባለፈ ጥራት ያለው የደም ባንክ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የሕክምና መሳሪያዎችና ግብዓቶችን ለክልል ደም ባንኮች እንደሚያቀርብ ተናግረዋል።

በደም ባንክ አገልግሎት ከባዱ ሥራ የደም ማሰባሰብ ሥራ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ ደም ማሰባሰብ ላይ በርካታ ግብዓቶች ያስፈልጋሉ። ድጋፍ የተደረጉት የሕክምና መሳሪያዎች በቀላሉ በሀገር ውስጥ ገበያ የማይገኙና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን፤ የክልል ደም ባንኮች የደም ማሰባሰብ ሥራቸውን ያቀልላቸዋል፤ ጥራቱን የጠበቀ የደም ልገሳ አገልግሎት እንዲያከናውኑም ያግዟቸዋል ብለዋል።

ከበጎ ፍቃደኛ ደም ለጋሾች የሚሰበሰበውን ደም ለመመርመር፣ ደህንነቱን ጠብቆ ለማስቀመጥ፣ የደም ተዋጽኦዎችን ለማምረትና ሌሎች ተግባራትን ማከናወን የሚያስችሉ 12 አይነት የሕክምና መሳሪያዎች ለ53 የክልል ደም ባንኮች ድጋፍ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

የአገልግሎቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ጤናዬ ደምሴ በበኩላቸው፤ የሕክምና መሳሪያዎቹ በሀገር ውስጥ የማይገኙ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የፈሰሰባቸው በመሆናቸው ባለሙያዎች በጥንቃቄ እንዲገለገሉና መሣሪያቸውን እንዳይናቸው ብሌን እንዲንከባከቡ አሳስበዋል።

# ከሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ አሽከርካሪዎች ተቀጡ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ ፡- ባለፉት ስድስት ወራት የትራፊክ ሕግን ተላልፈው የተገኙ ከሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ አሽከርካሪዎች እንደተቀጡ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴርን የስድስት ወራት እቅድ አፈጻጸም ሲገመግም በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ባለፉት ስድስት ወራት የትራፊክን ሕግ ተላልፈው የተገኙ ከሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ አሽከርካሪዎች ተቀጥተዋል። በዚህም ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ለመንግሥት ገቢ ሆኗል።




አሽከርካሪዎቹ የተቀጡት መደበኛና ድንገተኛ ቁጥጥር በማድረግ፤ በራዳር መሳሪያና በአልኮል መፈተሻ መሳሪያዎች በመጠቀም የትራፊክ ሕግ ተላልፈው በመገኘታቸው መሆኑን አንስተው፤ የጥፋት አይነቶችም የቴክኒክ ጉድለት፣ ደርቦ ማለፍ፣ ከፍጥነት በላይ ማሽከርከርና ከልክ በላይ መጫን በየደረጃቸው የሚጠቀሱ መሆናቸውን አንስተዋል። በሀገሪቱ ከሚደርሱት የትራፊክ አደጋዎች ከ60 በመቶ በላይ በአሽከርካሪ ስህተት የሚፈጸሙ መሆናቸውንም ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

የቅጣቱ አላማ ገንዘብ ማስገባት ሳይሆን አሽከርካሪዎች ሕግና ሥርዓት ይዘው እንዲያሽከረክሩ በማድረግ አደጋ መቀነስ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ በአሽከርካሪዎች ላይ የሚተላለፈው ቅጣት ከሌሎች ሀገራት አንጻር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ነው ብለዋል።

በአሽከርካሪ ለሚፈጸሙ ጥፋቶች መጨመር የቅጣቱ መጠን ዝቅተኛ መሆን የራሱ አስተዋጽኦ እንዳለው ጠቅሰው፤ ግንዛቤ የማስጨበጥና የማስተማር ሥራው እንደተጠበቀ ሆኖ ሕግ በሚተላለፉት ላይ የሚወሰደው ርምጃ ትምህርት በሚሰጥ መልኩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

በሀገሪቱ እየደረሰ ካለው የትራፊክ አደጋ 14 ነጥብ አምስት በመቶ የሚሆነውና ሁለተኛውን ደረጃ የያዘው በተሽከርካሪ ቴክኒክ ጉደለት የሚከሰት መሆኑን በማስታወስ፤ በተቋማቸው በኩል ጠንካራ ቁጥጥርና ርምጃ እየተወሰደ እንደሆነ ተናግረዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት 340 የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት እንዲሁም 87 የቴክኒክ ምርመራ ተቋማት ላይ የቁጥጥር ሥራ መከናወኑን ያስታወሱት ሚኒስትሩ፤ የ11 አሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፈቃድ የተሰረዘ ሲሆን 40ዎቹ ላይ ጊዜያዊ እገዳ መጣሉን ተናግረዋል። በተመሳሳይ ዘጠኝ የቴክኒክ ምርመራ ተቋማት እንደተሰረዙና ለሁለቱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጠ ገልጸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ እሸቱ ተመስገን (ዶ/ር) የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር የስድስት ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በቀረበበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ በትራፊክ አደጋ በርካታ ህይወት እየጠፋና የአካል መጉደልና ከፍተኛ የንብረት ውድመት እየተከሰተ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ በተሽከርካሪ የቴክኒክ ጉድለት የሚከሰተው አደጋ በሁለተኛ ደረጃነት ተቀምጧል።

ይህንን ለመቀነስ ተሽከርካሪዎች በየዓመቱ ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው ይታወቃል። ቁጥጥሩ መካሄድ ያለበት ከሰው ህይወትና ንብረት ውድመት ጋር በማስተያየት መሆን ቢኖርበትም አሁንም በቂ ምርመራ ሳይደረግ ፍተሻውን እንዳለፈ በማስመሰል ማረጋገጫ የሚሰጡ ተቋማት መኖራቸውን ጠቁመዋል። ይህ አካሄድ ለበርካቶች ህይወት ማለፍና ለአካል መጉደል ብሎም ለንብረት ውድመት ምክንያት እየሆነ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ሞዴል የአሽከርካሪና የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ተቋማት ለመፍጠር አበረታች ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም፤ ዛሬም ድረስ 25 በመቶ የሚሆኑት እየሠሩ ያሉት ከደረጃ በታች ነው። ይህም የትራፊክ አደጋን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ እንቅፋት ሆኗል ነው ያሉት።

ከዚህ መነሻነትም በተቋማቱ ላይ የሚደረጉ ቁጥጥሮች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚጠበቅባቸው አሳስበው፤ በዚህ ረገድ በመንግሥትና በተቋሙ በኩል አቅም ውስንነት ካለ ከግሉ ሴክተር ጋር በመቀናጀት ችግሩን ለመፍታት መሥራት ይጠበቃል ብለዋል።

## በክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት ለ54 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል

**አንተነህ ቸሬ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት ባለፉት ስድስት ወራት ለ54 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ መሰጠቱን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊና የኢንቨስትመንት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከበደ ተስፋዬ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፣ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ አራት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 77 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 54 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ወስደዋል። ለ37ሺህ 993 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፣ 37ሺህ 788 ዜጎችን የሥራ እድል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

የኢንቨስትመንት መሬት አቅምን በመለየት ረገድ፣ ስምንት ሺህ ሄክታር መሬት ለማጥናት ታቅዶ፣ ከሰባት ሺህ 635 ሄክታር በላይ መሬት መጠናቱን አንስተው፤ ከዚህ በተጨማሪም ዘጠኝ ሺህ 644 ሄክታር መሬት ለባለሀብቶች ለማስተላለፍ እቅድ ተይዞ፤ከ10ሺህ 400 ሄክታር በላይ መሬት እንዲተላለፍ መደረጉን ገልጸዋል።

አቶ ከበደ እንዳስረዱት፣ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመሆን በቴክኖሎጂ በታገዘ አሠራር የባለሀብቶችን መረጃ የማጥራት ሥራ ተሠርቷል። በዚህም የባለሀብቶች ቁጥር፣ የማልማት አቅም፣ የስምሪት ዘርፎችና ሌሎች መረጃዎች ተጣርተው እንዲደራጁ እና ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው ላሉ የአስተዳደር አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገዋል። ከባለሀብቶች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገዋል።

የአገልግሎት አሰጣጡንና የመሠረተ ልማት አቅርቦቱን ቀልጣፋና የተሻለ በማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን መጨመርና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ውጤታማነት ማሻሻል ተችሏል ያሉት ኃላፊው፤ የፕሮጀክት ግምገማ ሥርዓቱ አጭር እንዲሆንና ከባለሀብቶች የሚነሱ ቅሬታዎችም በፍጥነት እንዲፈቱ መደረጉን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ከበደ ገለጻ፤ በክልሉ የሚገኙ ባለሀብቶች በሚያከናውኗቸው የኢንቨስትመንት ተግባራት አማካኝነት የሥራ እድል ከመፍጠር በተጨማሪ፣ ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ። ባለፉት ስድስት ወራት ባለሀብቶችን በማስተባበር 55 ኪሎ ሜትር ተደራሽ መንገድ መሥራት ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪም፣ 900 የኅብረተሰብ ክፍሎች በቡና ልማት ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ ሆነዋል።

# በአማራ ክልል ከ48 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት እየተሠራ ነው

## - እስካሁን 262 ሺ 879 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ በበጋ መስኖ ከ48 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ እስካሁን 262 ሺ 879 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑ ተገለጸ።

የክልሉ ግብርና ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ የሆኑት አቶ አንተነህ ሰውአገኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ በገጸ ምድርም ሆነ በከርሰ ምድር ውሃ ትልቅ አቅም ያለው በመሆኑ ለበጋ መስኖ ምቹ ነው። አርሶ አደሩ በዓመት ዝናብ ብቻ በመጠበቅ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመስኖ ሁለት ሶስት ጊዜ ማምረት እንዲችል በመስኖ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ነው።

እንደ ክልል በ2017 ዓ.ም 342 ሺ 480 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ በማልማት 48 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ አንተነህ፤ እስካሁን ባለው የመስኖ ልማት 262 ሺ 879 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል። ይህም የእቅዱን 77 በመቶ ነው። የመስኖ ልማት በአንደኛ፤ ሁለተኛ፤ እስከ ሶስተኛ ዙር ግንቦት ወር ድረስ የሚከናወን መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ሕዝብ ግንኙነት ባለሙያው ገለጻ፤ በክልሉ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ያለው የበጋ መስኖ ስንዴ ነው። በክልሉ 254 ሺ 100 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለመሸፈን እቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ከዚህም 9 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል። እስሁን 183 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ በዘር ተሸፍኗል ነው ያሉት።

የበጋ መስኖ ስንዴ ሀገራዊ የልማት ፕሮጀክት መሆኑን የጠቆሙት አቶ አንተነህ፤ እቅዱን ለማሳካት ለአርሶ አደሩ የሞተር ፓምፕ እና የአፈር ማዳበሪያ ስርጭት በስፋት እየተካሄደ ነው። የበጋ መስኖ ስንዴ ምርት የጎርፍና የዝናብ ስጋት ስለሌለበት ከመኸር ምርት የተሻለ ምርታማ መሆኑን ጠቁመዋል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ የክልሉ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን የገለጹት የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያው፤ እስካሁን ባለው የመስኖ ልማት እንቅስቃሴ 219 ሺህ 42 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል። ከ171 ሺህ ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል። የምርጥ ዘር አቅርቦቱም በተመሳሳይ 256 ሺህ 816 ኩንታል ምርጥ ዘር መሰራጨቱን ገልጸዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## የግብርናውን ስኬት የሚያስቀጥሉ ተግባራት ተጠናክረው ይቀጥሉ!

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በድርቅ፣ ረሃብና ተረጂነት እንድትታወቅ ካደረጓት ምክንያቶች መካከል እንደ ሀገር በተለይም በግብርናው ዘርፍ ያሉ አቅሞችን ለይቶና አልምቶ ካለመጠቀም ጋር የተያየዘ ነው። በዚህም በዓለም ላይ ሰፊ የሚታረስ መሬት፣ ዓመቱን ሙሉ የሚፈስሱ ወንዞች እና ከፍ ያለ ቁጥር ያለው አምራች ኃይል ወይም ወጣት ይዞ የሚራብና እርዳታን የሚጠብቅ ሀገር ሆና ስትገለጽ ቆይታለች።

ይሄ የዘለቀው ግን ኢትዮጵያን የሚገነዘብ፣ ስለ ኢትዮጵያውያን ክብር የሚጨነቅ፣ የኢትዮጵያ ሀብት እና የኢትዮጵያውያን አቅም በልኩ የሚረዳ መሪ እስኪገኝ ነበር። እናም ይሄ በጊዜው እውን ሲሆን፤ ባለፉት አምስት እና ስድስት ዓመታት ብቻ በተሠሩ ዘርፈ ብዙ የግብርና ልማት ሥራዎች ታሪክን መለወጥ ያስቻለ ውጤት እና ለዓለም ምሳሌ የሆነ ስኬት ማስመዝገብ ተችሏል።

ምክንያቱም በእነዚህ ዓመታት በተለይም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነትና መሪነት ግብርናው የምግብ ዋስትና ማረጋገጫም፤ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ግብዓት አቅራቢም፤ የወጪ ንግድ አቅም ማሳደጊያም፣ የአካባቢ ጥበቃ የጀርባ አጥንትም እንዲሆን ማስቻልን ማዕከል ያደረገ ነበር።

መነሻውን የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥና የምግብ ሉዓላዊነትን እውን የማድረግ ዓላማን ማሳካት ላይ አተኩሮ የተጀመረው የስንዴ ልማት ኢንሼቲቭ ስኬቱ ከፍ ብሎ የሚገለጥ ነው። ምክንያቱም፣ ርምጃው ኢትዮጵያ ስንዴ ከውጪ የምትሸምትበትንና እርዳታም የምትጠብቅበትን ሂደት የሰበረ፣ እንደ ሀገርም ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴን ለውጪ ገበያ ማቅረብ፣ እንዲሁም በ“ኢትዮጵያን ኤይድ” ለጎረቤት ሀገር እርዳታን ማድረስ ያስቻለን አቅም ፈጥሯልና።

የስንዴ ልማቱ ግን ብቻውን ግንጥል ጌጥ ሆኖ የተተገበረና እየተተገበረ ያለ አልነበረም። ይልቁንም አጠቃላይ የሰብል ልማቱ ላይ ትኩረት በማድረግ የግብርናውን ዘርፍ ማዘመንን፣ ምርትና ምርታማነትንም ማሳደግን ማዕከል አድርጎ የተሠራበት ነው። በዚህም ነው ከለውጡ በፊት እንደ ሀገር ከ250 ሚሊዮን ያልዘለለው ዓመታዊ የሰብል ምርት፤ ዛሬ ላይ በዓመት 700 ሚሊዮን ኩንታል እንዲጠበቅ ያስቻለ አቅም እንዲፈጠር ያደረገው።

ይህ ግን ዝም ብሎ ያለጥረት የተገኘ ውጤት አልነበረም። ስኬቱ እንዲመዘገብ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛል። ለምሳሌ፣ የግብርና ሜካናይዜሽንን ማስፋት አንዱ ተግባር ሲሆን፤ በዚህም ግብርናው ከተበጣጠሰ እርሻ ወደ ኩታ ገጠም እርሻ እንዲሸጋገር ማድረግ፤ በትራክተር እያረሰ በኮምባይነር አርሽስተር ምርቱን እንዲሰበስብ እድል ተፈጥሮለታል። ለዚህም የግብርና ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ያስቻለ በሕግ የተደገፈ ርምጃ ተወስዷል።

ሌላኛው፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የምርጥ ዘርና ማዳበሪያን የመሳሰሉ ግብዓቶችን በብዛትም፣ በጊዜውም የማቅረብ ርምጃ ነው። በዚህ ረገድ ቀድሞ የነበረውን አሰራር በመለወጥ ማዳበሪያ በብዛትም፣ በወቅቱ አንዳንዴም ከወቅቱ ቀድሞ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ብቻ ሳይሆን ወደ አርሶአደሩ እንዲደርስ ማድረግ ተችሏል።

ለማሳያም ያህል፣ ለቀጣይ የበልግ፣ የመኸርና የመስኖ ልማት ሥራዎች የሚውሉ ማዳበሪያዎች ጭምር ዛሬ ላይ ወደብ ከመድረስ አልፈው ወደ ሀገር ውስጥ እየገቡ ይገኛል። የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተውም፣ ዩሪያ እና ዳፕ ማዳበሪያ የጫኑ ስድስት መርከቦች ጅቡቲ ወደብ የደረሱ ሲሆን፤ ወደብ ከደረሰው 313 ሺህ 260 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ 256 ሺህ 398.2 ሜትሪክ ቶን ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል።

በተጨማሪም 56 ሺህ ሜትሪክ ቶን ዳፕ የአፈር ማዳበሪያ የጫነች ሰባተኛ መርከብ ዶራሌ ሁለገብ ወደብ ደርሳ ጭነት እያራገፈች ሲሆን፣ በሚቀጥሉት ቀናትም ተጨማሪ አራት የአፈር ማዳበሪያ የጫኑ መርከቦች ጅቡቲ ይደርሳሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይሄ ደግሞ ለጉዳዩ ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው አመላካች ነው።

የምርጥ ዘር ብዜትና ሥርጭትን በተመለከተም፣ ዘርፈ ብዙ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፤ በፌዴራል ደረጃ ከሚከናወኑ ተግባራት ባሻገር ክልሎችም በራስ አቅም የምርጥ ዘር ፍላጎትን ለማሟላት እየሠሩ ነው። ለምሳሌ፣ በአፋር ክልል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ያለው የላቀ የሰብል ልማት በተለይም የስንዴ ኢንሼቲቭ ውጤታማነትን ከማስቀጠል አኳያ የተለያዩ የሰብል ዓይነቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬ እና የእንስሳት መኖ መሥራች እና ዋና የዘር ብዜቶች ሥራ በ700 ሔክታር ላይ እያከናወነ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ በ400 ሔክታር ላይ የሚባዛው የስንዴ ምርጥ ዘር ነው።

በዚህ መልኩ የግብርናውን ዘርፍ የማዘመንና ምርታማነቱን የማሳደግ ታዲያ በዓመት አንዴና ሁለቴ ያውም በዝናብ ላይ ተመስርቶ በሚፈለገው ልክ ሊጓዝ እንደማይችል ስለታመነበት፤ በዓመት ሦስቴ ማምረት የሚያስችል አሰራርን፣ ቆላ ተብለው ከምርት ተገናኝተው የማያውቁ ለም መሬቶችን ወደ ልማት የማስገባት ርምጃ ተወስዷል።

በዚህ በኩል ሰፋፊ የቆላማ አካባቢ ለም መሬቶችን ዓመቱን ሙሉ ከሚፈስሱ ወንዞች ጋር በማገናኘት በመስኖ የማልማት ሥራ በስፋት ተጀምሯል። ለዚህ ደግሞ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷቸው በአነስተኛ፣ በመካከለኛ እና በትላልቅ ደረጃ የሚገለጹ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች (ግድቦች) ተከናውነዋል። እየተከናወኑም ይገኛል።

ይሄ ደግሞ እንደየ መልክዓ-ምድራዊ እና እንደየክልሎች ተጨባጭ ሁኔታው በሁሉም አካባቢዎች እየተከወኑ ሲሆን፤ በዚህ መልኩ በትኩረት እየሠሩ ካሉ እና መልክዓ ምድራዊ ብዝሃነት ካላቸው ክልሎች መካከል የአማራ ክልል አንዱ ሲሆን፤ በክልሉ ከ12 ቢሊዮን ብር በላይ በጀት 158 የመስኖ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ነው። በዚህም የየአካባቢው አርሶአደሮች ተጠቃሚነትን ማሳደግ ተችሏል።

በአጠቃላይ ለግብርናው ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት፣ የተከናወኑ ተግባራትና የተገኙ ውጤቶች ስኬታማ መሆናቸው ታይቷል። ስለሆነም አሁን ላይ የሚያስፈልገው ነገር ስኬቶችን አተልቆ ማስቀጠል ነውና የተጀመሩ ስኬታማ ተግባራት ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የተፋሰስ ልማት ሥራው - ለግብርናው እድገት ተጨማሪ አቅም

**በየኔነው ስሻው**

ዓለማችን በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት፤ በአንድ በኩል ድርቅ፣ በሌላ በኩል ወጀብና አውሎ ንፋስ፣ አለፍ ሲልም በጎርፍ ማዕበል እየተመታች ውሎ ማደሩን ሥራዬ ብላዋለች። ይሄ ደግሞ በሰው ልጆች የሥራ ውጤት ምክንያት የተፈጠረባት ሲሆን፤ በተለይ የተፈጥሮን ሚዛን ጠብቆ ከተፈጥሮ አለመጠቀም ጋር በተያያዘ የተፈጠረ፤ ዛሬም እየተፈጠረ ያለ ችግር ነው።

በተለይ የሰው ልጆች ቁጥር መጨመር እና ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፍላጎትን ለማሟላት የሚደረጉ የግብርና እና የማዕድን ልማት ሥራዎችን ጨምሮ፤ የደን ውጤቶችን ጥቅም ላይ የማዋል ሂደቱ በእጅጉ ለአካባቢ ሥነምህዳር ጎጂ በሆነ አግባብ ሲከወን መቆየቱ መሬት እንድትራቆት ምክንያት ሆኗል።

ምክንያቱም እርሻ በሰፋ ቁጥር ደኖች እየተጨፈጨፉ ይሄዳሉ፤ የማዕድን ፍለጋ ሂደቱም ቢሆን ለደን መጨፍጨፍም ሆነ ለአፈር ጥበቃ ሥራ ትኩረት የሚሰጥ አይደለም፤ የደን ውጤቶችን በተለያየ አግባብ (ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለጣውላ፣ ለቤት መሥሪያና ለሌሎችም ግልጋሎቶች) ጥቅም ላይ የማዋል ሂደቱም የነበረውን ከማመናመን ያለፈ በጎደለው ቦታ የመተካት ልምምድ የሌለው ነው።

በዚህም የተነሳ የዓለማችን የደን ሽፋን በእጅጉ ተመናምኗል፤ ዓለም ሳንባዋ በአማዞን ደን ላይ እንዲንጠለጠል አድርጓል፤ በአንድ በኩል ዝናም እንዲበዛ በማድረግ የከፋ ጎርፍና ማዕበል እንዲከሰት፤ በሌላ በኩል ዝናብ እንዲያጥር በማድረግ ድርቅና ሰደድ እሳት እንዲፈጠር እያደረገ ይገኛል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም፣ ዜጎች ለስደት፣ ለረሃብና ለጤና ችግር እየተዳረጉ ሲሆን፤ በተለይ ችግሩ በፈጠረው የጎርፍና የድርቅ ችግሮች መፈራረቅ ምክንያት የግብርና ሥራ ላይ ያለው አሉታዊ ተጽዕኖው እየጎላ መጥቷል። ምክንያቱም ግብርና ተስማሚ ሥነ ምህዳርን ይፈልጋል። ይሄ ተስማሚነት በሌለበት እና ድርቅ ወይም ማዕበል በሚፈራረቅበት ሁኔታ በእጅጉ ይፈተናል።

ይሄን መነሻ በማድረግም እንደ ዓለም የአየር ንብረት ተጽዕኖን ለመቋቋም የሚያስችል ስትራቴጂ ተቀምጦ እንዲተገበር እየተደረገ ሲሆን፤ ሀገራትን እንደየአከባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ይሄን ኢኒሼቲብ ተቀብለው እየተገበሩ ይገኛል። ይሁን እንጂ አተገባበሩና ኢኒሼቲቪ የሚጠይቀውን ኃላፊነት ከመወጣት አኳያ ያለው ተነሳሽነትና አፈጻጸም በእጅጉ የተለያየ ነው። በተለይ ለአየር ንብረት ለውጥ መከሰት ትልቁን ሚና እና ድርሻ ካላቸው የበለጸጉት ሀገራት የሚጠበቅ ኃላፊነትን የመወጣት ሂደቱ እጅጉን ደካማ ሆኖ ይታያል።

በአንጻሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ለችግሩ እምብዛም አበርክቶ የሌላቸው፤ ነገር ግን የችግሩ ከፍ ያለ ተጠቂ የሆኑ ሀገራት እያደረጉ ያለው ጥረት የሚበረታታ ቢሆንም፤ ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል አቅምን የሚፈጥርላቸው ድጋፍ ካለማግኘት ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ልክ እንዳይጓዙ እንቅፋት ሲሆንባቸው ይታያል።

ይሁን እንጂ፣ ለችግሮች ሳይንበረከኩና የሌሎችን ዳረጎት ሳይጠብቁ ከሚሠሩ ሀገራት በቀዳሚነት የምትቀመጠው ኢትዮጵያ፤ በዚህ መልኩ የምታከናውነው ተግባር በተለይ ባለፉት ስድስት ዓመታት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ታግዞ በእጅጉ ውጤት የታየበት ሆኗል።

ይሄ ውጤት የታየው እንደ ሀገር ከፍተኛ በጀት መድቦ በመሥራት አይደለም። ይልቁንም የሀገር አንድ አቅም የሆነውን ሰፊውን ሕዝብ አስተባብሮ በመሥራት ነው። በዚህም በቢሊዮን የሚገመት በጀት ሊሠራው የማይችለውን ሥራ በሚሊዮኖች ትብብር እውን ማድረግ ተችሏል። በተለይ በአረንጓዴ ዐሻራው መርሃ ግብር ዓለም ያላደረገውን በስምንት ዓመት ከ50 ቢሊዮን ችግኞች በላይ የመትከል ግብ ተቀምጦ በተሠራው ሥራ፣ በአንድ ጀንበር ከ600 ሚሊዮን የላቁ ችግኞችን በመትከል አዲስ ታሪክ መጻፍ ያስቻለ ውጤት ተገኝቶበታል።

ይሄ ተግባር ታዲያ እንደ ሀገር ቀድሞ የነበረውን 40 በመቶ የደን ሽፋን አመንምኖ ወደ ሦስት በመቶ በታች አውርዶት የነበረውን ችግር መቀልበስ እና ዛሬ ላይ የደን ሽፋኑን ከ23 በመቶ በላይ ማድረስ ያስቻለ ስኬትን አሳይቶናል። ከዚህም ባለፈ፣ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሩ ሥራ፣ የግብርናው ዘርፍ አንድ አቅም ሆኖ የታየበት ነበር።

> **በመርሃ ግብሩ የሚተከሉ ችግኞች የደን ሽፋንን ብቻ ለማሳደግ ሲባል የሚከወኑ ሳይሆን፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ፤ ለወጪ ንግድ እድገት እና ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ የችግኝ ዝርያዎች በስፋት እንዲካተቱ የተደረገበት ነው። በዚህም ቡናን ጨምሮ የተለያዩ የፍራፍሬ ዓይነቶችም ተክለውበታል፤ ዛሬ ላይ ለውጤት በቅተዋል**

በተለይ በመርሃ ግብሩ የሚተከሉ ችግኞች የደን ሽፋንን ብቻ ለማሳደግ ሲባል የሚከወኑ ሳይሆን፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ፤ ለወጪ ንግድ እድገት እና ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ የችግኝ ዝርያዎች በስፋት እንዲካተቱ የተደረገበት ነው። በዚህም ቡናን ጨምሮ የተለያዩ የፍራፍሬ ዓይነቶችም ተክለውበታል፤ ዛሬ ላይ ለውጤት በቅተዋል።

ለምሳሌ፣ መርሃ ግብሩ ሲጀመር የተተከሉ የቡና ችግኞች ዛሬ ላይ ለቡና የወጪ ንግድ እድገት አቅም ሆነዋል። በተመሳሳይ ፓፓዬ፣ ብርቱካን፣ አቮካዶ፣ ሙዝና የመሳሰሉት የፍራፍሬ ዓይነቶች በስፋት በመርሃ ግብሩ እንዲተከሉ በመደረጉ፤ ምርቶቹ ለሀገር ውስጥ ፍጆታም፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነትም፤ ለወጪ ንግድ እድገትም አቅም ሆነዋል።

አቮካዶን እንደ አብነት ብናይ፤ አቮካዶ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እየዋለ ነው፤ ለዘይት እና ቅባት ኢንዱስትሪዎችም ግብዓት እየሆነ ነው፤ ለውጪ ገበያም እየቀረበ ነው። በመሆኑም በአረንጓዴ ዐሻራው መርሃ ግብር እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች የአካባቢን ሥነምህዳር ከመጠበቅ ባሻገር፤ የግብርናው ዘርፍ አቅም ሆነው እየተገለጡ ያሉ ናቸው።

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ እንግዳ

## «ፋይዳ መታወቂያ ሌሎቹን መታወቂያዎች የሚተካ አይደለም»

- አቶ ዮዳሄ አርአያሥላሴ
የፋይዳ ብሔራዊ መታወቂያ ዋና አስተባባሪ

እስማኤል አረቦ

ዓለማችን በተለያየ የእድገት ሂደት ውስጥ ስትጓዝ ቆይታለች፡፡ ግብርና የመጀመሪያውን የሰው ልጅ ሥልጣኔ ያመጣ ሲሆን በተራው ደግሞ የተሻለ ካፒታልና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለሚሻው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ቦታውን አስረክቧል፡፡ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በርካታ ሀገራትን ለዕድገትና ለብልፅግና አብቅቷል፤ የተሻለ የአኗኗር ሥርዓትን ፈጥሯል፡፡ አሁን ደግሞ ዘመኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመን ነው፡፡ ዘመነ ዲጅታላይዜሽን ዓለም በየዕለቱ አዳዲስ ክስተቶችን እንድታስተናግድና በፍጥነት እንድትጓዝ እያደረጋት ይገኛል፡፡

ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን በማቀላጠፍ፤ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራትና ገንዘብ፤ ጊዜንና ጉልበትን በመቆጠብ ለአንድ ሀገር ዕድገትና ብልፅግና የማይተካ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይም በአሁኑ ጊዜ የአገልግሎት አሰጣጥም ሆነ የኢኮኖሚ ዝውውሩ በቀጥታ የታያዘው ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂው ጋር በመሆኑ የሀገራት ዕድገትም ሆነ ውድቀት ለዘርፉ በሰጡት ትኩረት ልክ የሚለካ ነው፡፡

ይህንኑ እውነታ በመገንዘብም ኢትዮጵያ ከአምስቱ የዕድገት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲሆን ፈቅዳ ወደ ሥራ ገብታለች፡፡ "ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" ስትራቴጂን በመቅረጽም ሀገሪቱ በሁሉም መስክ ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚን ለመገንባት ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ ስትራቴጂም በዋናነት የዲጂታል መሠረተ ልማት በመገንባት እና በማስፋት የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ማፋጠንን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ትኩረት ሰጥታ እየተገበረች ያለችው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ የመንግሥትን አገልግሎት በዲጂታል የታገዘ እንዲሆን በማድረግ ዜጎች ባሉበት ሆነው የመንግሥትን አገልግሎቶች በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡ የዜጎች የዕለት ተዕለት ሕይወት እንዲቀላጠፍም መሠረት ይጥላል፡፡

ለዚህ አንዱ መሠረት የሚሆነው ደግሞ ብሔራዊ መታወቂያ(ፋይዳ) የተሰኘው የመታወቂያ ዓይነት ነው፡፡ ፋይዳ መታወቂያ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ለዜጎች እየተሰጠ ይገኛል፡፡ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም የፋይዳ መታወቂያ ምንነት፤ ሀገራዊ ጠቀሜታ እና ዜጎች የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻር ያለው ጥቅም ምንድን ነው ስንል ለፋይዳ ብሔራዊ መታወቂያ ዋና አስተባባሪ ለአቶ ዮዳሄ አርአያሥላሴ ጥያቄዎችን አቅርበናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡



ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- የብሔራዊ መታወቂያ አጀማመር ዓለም አቀፍ ተሞክሮን ከማየት ብንጀምር?**

**አቶ ዮዳሄ፡-** የመታወቂያ ወረቀትን እንደ መተማመኛ የተጠቀሙት ስዊዘርላንዶች ናቸው፡፡ ስዊዞች ይህንን ማድረግ ያስፈለጋቸው ደግሞ የሰዎች ዝውውር የተቀላጠፈ እንዲሆንና የንግድ ልውውጡም የሰፋ እንዲሆን ከማሰብ ነው፡፡ በተወሰነ አካባቢ ታጥሮ የነበረውን የሰዎች እና የሸቀጦች ዝውውርን በፈጠሩት መታወቂያ የተነሳ ወደ ሰፊ አካባቢ ማዳረስ ችለዋል፡፡

ቀረብ ወዳለው ጊዜ ስንመጣ ደግሞ አሜሪካኖች ሶሻል ሴኩሪቱ ቁጥር ከጀመሩ 100 ዓመታት አልፏቸዋል፡፡ 1900 ላይ አሜሪካ ውስጥ እያንዳንዱ አሜሪካዊ የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር ነበረው፡፡ እያንዳንዱ ሰው የወረቀት መታወቂያ ማሳየት አይጠበቅበትም፡፡ መለያ የሆነውን ቁጥር በማሳየት ብቻ ማንነቱን መግለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ትራፊክ ቢያስቆመው መንጃ ፍቃድ ወይም መታወቂያ ሳያስፈልገው መለያ የሆነውን ቁጥር በመንገር ብቻ ከትራፊኩ ጋር መግባባት ይችላል፡፡ እኛ ሀገር ሲደረግ እንደቆየው አንድ ሰው የትራፊክ ጥሰት ቢፈጽም ታርጋውን መንቀል ወይም መንጃ ፈቃዱን መንጠቅ ሳያስፈልግ በሰውዬው መለያ ቁጥር በመግባት አስፈላጊውን ቅጣት መቅጣት ይችላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ብሔራዊ መታወቂያ እንዲኖር ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ ዮዳሄ፡-** ኢትዮጵያ 1284/2015 የዲጂታል መታወቂያ አዋጅን አጽድቃለች፡፡ ይህ አዋጅ ያስፈለገበት ምክንያት በመግቢያው ላይ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ ዲጂታል መታወቂያ በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከብሔራዊ ደህንነት፤ ከመልካም አስተዳደር፤ ከሥራ ቅልጥፍና፤ ከኢኮኖሚ እድገት እና ከመሳሰሉት አንጻር ዲጂታል መታወቂያ የማይተካ ሚና ይጫወታል፡፡ አሁን ከደረስንበት ዓለም አቀፋዊም ሆነ ሀገራዊ ሁኔታ አንጻር ያለ ዲጂታል መታወቂያ እድገትን ማረጋገጥ አንችልም፡፡

ቴክኖሎጂ ዓለምን እየቀየረ ነው፡፡ የተቀየረ ዓለም ደግሞ የተቀየረ አሠራር ይፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል በወረቀት ሲሰጡ የነበሩ አገልግሎቶች በሙሉ አሁን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ውስጥ ገብተው ሰው ባለበት ሆኖ አገልግሎቱን የሚያገኝበት አገልግሎት እውን ሆኗል፡፡ ቀደም ሲል ሰዎች መንግሥታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ቀበሌ ወይም ሌላ አንድ መንግሥታዊ ተቋም የመሄድ ግዴታ ነበረባቸው፡፡ ዛሬ ግን አገልግሎቱ ቤታቸው ድረስ እየመጣ ነው፡፡ ፊት ለፊት አገልግሎት ሰጪና ተቀባይ የሚገናኙበት አሠራር እያበቃለት ነው፡፡ ውል የሚፈጽሙ ሰዎች እንኳን ‹‹እርጥብ ፊርማቸውን ካላስቀመጡ ውሉ የጸና አይሆንም›› የሚለው የተለመደ አባባል ቀርቶ ዛሬ ዲጂታል ፊርማ እውን ሆኗል፡፡

መታወቂያንም በተመለከተ በርካታ ሀገራት ከወረቀት በመላቀቅ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ተሸጋግረዋል፡፡ ለዘመናት ስንገለገልበት የቆየነው በቦርሳችን ይዘናት የምንዞረው መታወቂያ በብዙ ሀገራት እየቀረች መጥታለች፡፡ በምትኩ የወረቀት ሕትመት ሳይኖር ቁጥር ብቻ የአንድ ሰው መታወቂያ ለመሆን በቅቷል፡፡ የወረቀት መታወቂያ ለበርካታ ማጭበርበሮች የተጋለጠ ነው፡፡ በቀላሉ ፎርጅድ ስለሚሠራም ዜጎችም ሆኑ ሀገር ለኪሳራ ይጋለጣሉ፡፡

ፎርጅድ በተሠራ መታወቂያ ከባንክ ገንዘብ ይወጣል፤ መሬት ካርታ ይሸጣል፤ ግብር ይጭበረበራል፤ አንድ ሰው ሆኖ በበርካታ ስሞች በርካታ መታወቂያዎችን፤ የንግድ ፍቃዶችን ማውጣት እና የፈለገውን ወንጀል መሥራት ይችላል፡፡ ዛሬ ግን ይህ ሁሉ አክትሞለታል፡፡ የፊት ዐሻራን ብቻ በመውሰድ ግለሰቡ የትም ቢሄድ የሚታወቅበት አሠራር ተዘርግቶ እየተሠራበት ነው፡፡ የፋይዳ መታወቂያም አንዱ ጥቅም ይሄ ነው፡፡

እንደ ቀድሞ ‹‹እኔ ሳላውቅ የባንክ አካውንቴ ውስጥ ገብተው ገንዘቤን አጭበረበሩኝ፤ ፎርጂድ የመሬት ካርታ ሰጡኝ፤ ወዘተ›› የሚሉ አቤቱታዎችን በፋይዳ መታወቂያ መፍታት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ፋይዳ መታወቂያ አገልግሎትን ለማሳለጥ እና ዜጎች ለሙስና እንዳይጋለጡ ያደርጋል፡፡ ለአብነት አንድ ሰው የቤት ኪራይ ውል ለመፈጸም ቀበሌ ወይም ወረዳ መሄድ ይኖርበታል፡፡ እዚያ ቁጭ ብሎ ወረፋ መጠበቅ እና መውጣት መውረድ ግድ ይለዋል፡፡ በዚህ ሂደት ቢያንስ ቢያንስ ግማሽ ቀን ይወስድበታል፡፡

ይህ ደግሞ ሰውን ያማርራል፤ ሥራ ያስፈታል፤ ሰውዬው ምርታማ ሆኖ ሕይወቱን እንዳያሻሽል እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ይሄን ኋላቀር አሠራር ልንቀርፈው እና በቶሎ ልንሻገረው የሚገባ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ፋይዳ መታወቂያ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ፋይዳ መታወቂያ ከባሕላዊ አሠራር ወደ ዘመናዊ አሠራር የሚወስደንን መንገድ የሚመቻች እና የሰዎችንም እንግልት ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት የሚያፋጥን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ብሔራዊ መታወቂያ የሕዳሴ ግድብ ያህል ሀገራዊ ፋይዳ አለው ሲሉ ተናግረዋል፡፡ ምን ማለታቸው ነው?**

**አቶ ዮዳሄ፤-** ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሄንን ያሉት ብሔራዊ መታወቂያ ያለውን ሀገራዊ ጥቅም በአግባቡ ስለሚያውቁት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ወደ ዲጂታላይዜሽን ባለመግባቷ ምክንያት እያጣች ያለችው ሀብት ከፍተኛ ነው፡፡ በየዕለቱ በሚደረጉ ማጭበርበሮች፤ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ያሉ ውጣውረዶች፤ በተደጋጋሚ ንግድ ፍቃዶች የሚሠሩ ደባዎች እና ግብር ስወራዎች፤ ከመሬት ጋር ያሉ ሌብነቶች እና ብልሹ አሠራሮች እና የመሳሰሉት ወደ ኢኮኖሚው ቢመነዘሩ ከፍተኛ ሀብት ለሀገር እና ለሕዝብ የሚያስገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሀብቶች በትክክለኛው መንገድ ወደ ኢኮኖሚው ቢገቡ በርካታ ልማቶችን ለማከናወን የሚያስችሉ ናቸው፡፡

ለአብነት አንድ ምሳሌ ላንሳ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ 2ነጥብ 3 ሚሊዮን የመንግሥት ሠራተኛ አለ፡፡ ይህ ሠራተኛ በቁጥር ይገለጽ እንጂ በአካል ይገኝ፤ አይገኝ ለማወቅ ያስቸግራል፡፡ በማኑዋል አሠራር በየክልሉ ባሉ ተቋማት ያሉ ሠራተኞችን ጥርት አድርጎ ለማወቅ ያስቸግራል፡፡ ወደ ነጋዴውም ስንመጣ ሰዎች በሠሩት ልክ አለመክፈል እና ጭራሹንም ሰዎች ከነገዱ በኋላ አድራሻቸውን መሰወር የተለመደ ሆኗል፡፡ ከሕግ አንጻር ብንመለከተው አንድ ጥፋት ያጠፋ ሰው የፍርድ ሂደቱን ጨርሶ ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ የሚታሰረው ሰው ግን ሌላ ሊሆን ይችላል፡፡ በገንዘብ ወይም በመደለያ አጥፊው ሌላ ታሳሪው ሌላ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡

በሌላም በኩል አንድ ሰው ሁለት ቦታ ተመሳሳይ ክስ የሚመሰረትበት አጋጣሚ አለ፡፡ በአንድ ጉዳይ አዳማ እና አዲስ አበባ ክስ መስርቶ ሊከራከር ይችላል፡፡ሕጉ የሚፈቅደው ግን በአንድ ጉዳይ አንድ ክስ ብቻ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው ተደጋጋሚ ወንጀል ፈጽሞ እሱ መሆኑን ለመለየት ችግር የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ የተለያዩ ወንጀሎችንም ፈጽሞ ከተማ እየቀያየረ መኖር ይችላል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት በዘመናዊ አሠራር ነው፡፡ ኢትዮጵያ የጀመረችውም ብሔራዊ መታወቂያ ይህንን ችግር የማስወገድ ብቃት አለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የፋይዳ መታወቂያ ከሌሎች የመታወቂያ ዓይነቶች በምን ይለያል?**

**አቶ ዮዳሄ፡-** በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ያሉት የመታወቂያ ዓይነቶች ሁለት ዓይነት ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡ አንደኛው ማንነትን የሚገልጸው በተለምዶ የቀበሌ መታወቂያ ሲሆን ሁለተኛው አገልግሎት ተኮር የሚባለው ነው፡፡ ይህም እንደ ፤ የመንጃ ፍቃድ፤ ፓስፖርት እና የመሳሰሉትን የሚያካትት ይሆናል፡፡ እነዚህም አገልግሎት የሚሰጡት በዋናነት ለተዘጋጁላቸው ጉዳዮች ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ የፋይዳ መታወቂያ ዓይነት ያለው አላማ የያዘ መሠረታዊ መታወቂያ ግን እስካሁን በሀገሪቱ አልነበረም፡፡ መሠረታዊ መታወቂያ ማለት የአንድን ሰው ማንነት በልዩነት ማሳየት የሚያስችልና ሁሉንም ዓይነት የመንግሥትና የግል አገልግሎቶች በአንድ መታወቂያ ሊያስጠቅም የሚያስችል ማለት ነው፡፡ የፋይዳ መታወቂያ ከየትኛውም የሀገሪቱ ቦታ እና የማህበረሰብ ክፍል የሚመጡ ዜጎችን አካታች በሆነ መልኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ይሆናል፡፡ መታወቂያው በሀገር ውስጥ ላሉ ዜጎች ብቻ ሳይሆን ከሀገር ውጪም በመኖሪያ ፈቃድ፤ በሥራ ፈቃድ፤

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ወቅታዊ እንግዳ

## «ፋይዳ መታወቂያ...

ከገጽ 6 የዞረ

በትምህርትና ሌሎች ጉዳዮች ከሀገር የወጡትንም ተጠቃሚ ያደርጋል። በተጨማሪ የውጭ ሀገር ሰዎችንና ስደተኞችንም የሚያካትት ይሆናል።

ፋይዳ መታወቂያ በብሔራዊ ደረጃ ወጥ የሆነ ይዘቶች ያሉት እና የትም የሚያገለግል ነው። ምሳሌ የአዲስ አበባ መታወቂያ አብዛኛው አገልግሎት የሚሰጠው ለአዲስ አበባ እና አካባቢው ነው። ፋይዳ መታወቂያ በርካታ መረጃዎችን በአንድ ላይ የያዘ እና ከግለሰቦች የሚሰበሰቡት መረጃዎችም ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶችን ያሟላ ነው። ሆኖም ፋይዳ መታወቂያ ሌሎችን መታወቂዎች ይተካል ማለት አይደለም። ፋይዳ መታወቂያ ከሌሎቹ መታወቂያዎች ጋር እንዲናበብ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው እንጂ ሌሎችን መታወቂያዎች የሚተካ አይደለም። ፋይዳ መታወቂያም አገልግሎት እየሰጠ ሌሎችም መታወቂያዎች አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ ማለት ነው።

አንድ ምሳሌ ባነሳ፤ ‹‹ቲን ነምበርህን ካላመጣህ ንግድ ፈቃድህን አላድስልህም፤ ወይም የመንጃ ፈቃድ ቁጥርህን ካላስታወስከው መንጃ ፈቃድህ አይታደስም›› የሚለው ክልከላ ከዚህ በኋላ አይኖርም። ‹‹የመሬት ይዞታን ለማረጋገጥ ካርታ ይዘህ ና የሚለው›› አባባል ይቀራል ማለት ነው። ፋይዳ መታወቂያ ዲጂታል ስለሆነ እና ከተለያዩ አገልግሎቶች ጋር የተሳሰረ በመሆኑ የፋይዳ ቁጥርን በማስገባት ብቻ ሁሉንም አገልግሎቶች ማግኘት ያስችላል። በሌላ አነጋገር አንድ ሰው የፋይዳ ቁጥሩን ተናግሮ ብቻ ሁሉንም አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችለው እና ፋይል ይዞ ከመዞር የሚያወጣው ነው። ስለዚህም ፋይዳ መታወቂያ የዜጎችን ሕይወት ያቀላል ማለት ነው።

በቀጣይ መንጃ ፈቃድ ለማደስ በአካል መገኘት አያስፈልግም። በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ ሰው ቤቱ ቁጭ ብሎ ስልኩ ላይ መንጃ ፈቃድ ማደስ የሚችልበት ደረጃ ላይ እንደርሳለን። ጎረቤት ሀገር ኬንያ እኮ መንጃ ፈቃድ የሚታደሰው ስልክ ላይ ነው። ኢትዮጵያም ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ያለችው አገልግሎቶችን ከሰው ንክኪ ነፃ ለማድረግ ነው። በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ በርካታ አገልግሎቶች ከሰው ንክኪ የጸዱ ይሆናሉ። ይህ ሲሆን አገልግሎቶችን በገንዘብ መግዛት፤ ጉቦ መስጠት፤ መውጣት መውረድ፤ ለአንድ አገልግሎት ቀን ሙሉ መዋል እና የመሳሰሉት እንግልቶች ይቀራሉ። በዚህም የዜጎች እርካታ ይጨምራል፤ በመንግሥት ላይ ያላቸው እምነት ይጨምራል።

ከላይ እንደገለጽኩትም የተለያዩ ወንጀሎችን ሰርቶ መሸሸግ አይችልም። ስለዚህም አንድ ሰው ወንጀል ሰርቶ መሸሸግ እንደማይችል ስለሚያውቅ ወንጀል ከመሥራት መቆጠቡ አይቀርም። አንድ ሰው በተለያዩ ስሞች የተለያዩ ንግድ ፈቃዶችን በማውጣት ሊያጭበረብር አይችልም። ከግብር ስወራ ጋር በተያያዘም መንግሥት ትክክለኛውን ግብር እንዲያገኝ ያስችለዋል። አንድ ሰው የመሬት ካርታ ቢጠፋበት አሁን ባለው አሠራር መሬት አስተዳደር ሄዶ፤ አመልክቶ ቢያንስ ሶስት ወራት መጠበቅ አለበት። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ግን ሰዎች ከስልካቸው የመሬት ካርታቸውን አውርደው ለሚፈልጉት ዓላማ ማዋል ይችላሉ። የተጭበረበረ የመሬት ካርታ የመሳሰሉት የማጭበርበሪያ ስልቶች ሊኖሩ አይችሉም።

በፋይዳ መታወቂያ ሙሉ ለሙሉ ጥርጣሬዎች እና ማጭበርበሮች ይቀራሉ። ፋይዳ መታወቂያ የመተማመኛ ማሕቀፍ ነው ሲባል ጥርጣሬዎችን እና ማጭበርበሮችን ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ ስለሚያስችል ነው። ሰነድ ጠፋ፤ ሰነድ ተሰወረ የሚሉ አባባሎች ሙሉ ለሙሉ ይቀራሉ ማለት ነው። ሌሎቹ መታወቂያዎች ግን ይህንን የማድረግ አቅም የላቸውም።

**አዲስ ዘመን:- በአሁኑ ወቅት የብሔራዊ መታወቂያ ለምን ያህል ዜጎች ተዳርሷል ?**

**አቶ ዮዳሄ:-** የፋይዳ መታወቂያ በሀገር አቀፍ ደረጃ መሰጠት የተጀመረው በ2015 ዓ.ም ነው። አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ 11 ሚሊዮን ዜጎች የብሔራዊ መታወቂያ ወስደዋል። በ2017 መጨረሻ ደግሞ 30ሚሊዮን ዜጎች የብሔራዊ መታወቂያ እንዲያገኙ እየተሠራ ነው። የሰዎች ግንዛቤ እየተሻሻለ በመምጣቱ የብሔራዊ መታወቂያ ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎት አለ። አብዛኛው ኢትዮጵያ የብሔራዊ መታወቂያ እንዲኖረው ይፈልጋል። ሆኖም ከላይ እንደጠቀስኩት በማጭበርበር እና በወንጀል ውስጥ መቆየት ከሚፈልጉት ጥቂት ሰዎች በስተቀር ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚባል መልኩ የብሔራዊ መታወቂያ ባለቤት ለመሆን ከፍተኛ ፍላጎት አለው። በአሁኑ ወቅትም በሁሉም ክልል እና ከተማ አስተዳደሮች ብሔራዊ መታወቂያ እየተሰጠ ነው።



**የብሔራዊ መታወቂያ ተግባራዊ መደረጉ በኢትዮጵያ ላይ የ7 በመቶ ተጨማሪ ዕድገት ለማስመዝገብ ያስችላል። አሁን ኢትዮጵያ 200 ቢሊዮን ዶላር በላይ ዓመታዊ ጂዲፒ ያላት ሀገር ነች። ስለዚህ የዚህን ሰባት በመቶ ተጨማሪ ሀብት ማስገኘት ያስችለናል ማለት ነው**

ሆኖም እዚህ ጋር የሚታዩ ክፍተቶችን ማረም ይገባል። አንዳንድ ባንኮች አካውንት ቁጥር ካልከፈታችሁ ፋይዳ መታወቂያ አንሰጣችሁም የሚሉ ቅድመ ሁኔታዎችን እንደሚያስቀምጡ ደርሰንበታል። ይሄ አግባብ አይደለም። ፋይዳ መታወቂያን ለማግኘት የሚቀመጥ ቅድመ ሁኔታ የለም።

**አዲስ ዘመን:- ሰዎች ብሔራዊ መታወቂያ ባለማውጣታቸው የሚከለከሉ አገልግሎቶች አሉ?**

**አቶ ዮዳሄ:-** በጣም ጥቂት ከሆኑ አገልግሎቶች በስተቀር አብዛኛው አገልግሎት የብሔራዊ መታወቂያን የግድ የሚሉ አይደሉም። ከግብር፤ ሴፍቲኔት፤ ከመሳሰሉት እና ለመጭበርበር የተጋለጡ ዘርፎች ካልሆኑ በስተቀር አገልግሎት ለማግኘት የብሔራዊ መታወቂያ ግዴታ አይደለም። በክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የዲጂታል ካውንስል የሚባል አለ፤ ይህ ካውንስል በብሔራዊ መታወቂያ አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን እየለየ በየጊዜው ማስተካከያ እየሰጠ ስለሚሄድ ችግሮች ከስር ከስሩ እየተቃለሉ ይሄዳሉ። ሆኖም ብሔራዊ መታወቂያ ካላወጣችሁ አገልግሎት አታገኙም የሚሉ ተቋማት ካሉ አሠራራቸው ትክክል ስላልሆነ ሊያስተካክሉ ይገባል።

**አዲስ ዘመን:- በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ፋይዳ መታወቂያን ለማግኘት ረጃጅም ሰልፎች ይታያሉ፤ ከምን የመነጨ ነው ?**

**አቶ ዮዳሄ:-** መጀመሪያ መታወቅ ያለበት ፋይዳ ቁጥር ነው። አገልግሎትም ለማግኘት የሚያስፈልገው ቁጥር እንጂ ካርዱ አይደለም። ካርዱ በፍላጎት የሚወጣ እንጂ አስገዳጅ አይደለም። ያው፤ ብዙዎቻችን መታወቂያ ሲባል የምናገናኘው ከካርድ ጋር ስለሆነ እንጂ ካርድ ማሳተም ግዴታ አይደለም። የሰውዬው መለያ ቁጥሩ እንጂ ካርዱ አይደለም። ስለዚህም ከወረቀት አስተሳሰብ መውጣት አለብን። የፋይዳን መታወቂያ ለማሳተም ወረፋ መጠበቅ የለብንም። ካርዱን ሳያሳትሙ በቁጥሩ ብቻ መገልገል ይቻላል።

ለምሳሌ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት አንድ ሰው ንግድ ቢሮ ሲሄድ የሚጠየቀው ቁጥሩን እንጂ ካርዱን መሆን የለበትም። የሰውዬው መታወቂያ ቁጥሩ እንጂ ካርዱ አይደለም። ካርድ ማሳተም እንደመስፈርት መቀመጥ የለበትም። የፋይዳ መታወቂያ ቁጥር እንጂ ካርድ አይደለም። ስለዚህም መሰለፍ እና ጊዜ ማባከን አይገባም። በተለይ በአሁኑ ወቅት ሁሉም የቴሌ እና የፖስታ ቤት እንዲሁም ፍቃድ ያገኙ ተቋማት አገልግሎቱን እየሰጡ ስለሆነ ሰዎች አቅራቢያቸው ወደሚገኙ አገልግሎት ሰጪዎች በመሄድ ያለ ሰልፍ መገልገል ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን:- አንዳንድ ተቋማት ቴሌና ፖስታ ቤትን ጨምሮ ካርድ በክፍያ ይሰጣሉ፤ ይህ አግባብ አይደለም ማለት ነው?**

**አቶ ዮዳሄ:-** ይህ ግለሰቦች የፍላጎት ጉዳይ ነው። ከፈለጉ ካርድ አሳትመው መያዝ ይችላሉ፤ ካልፈለጉም ቁጥሩን በቃላቸው ይዘው ማንኛውንም አገልግሎት ማግኘት መብታቸው ነው። ግለሰቦችን ጨምሮ አንተም እንደጠቀስከው ቴሌ እና ፖስታ ቤት ጭምር ካርድ እያተሙ ይሰጣሉ። ይሄ ምንም ችግር የለውም። ካርድ እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ሰዎች ቢፈልጉ ከግለሰቦች አሊያም ከቴሌም ሆነ ፖስታ ቤት አሳትመው መጠቀም መብታቸው ነው። ሆኖም አንዳንድ ግለሰቦች ፎቶ ሾፕ በመሥራት ሀሰተኛ መታወቂያ እንደሚያትሙ መረዳት እና መጠንቀቅ ይገባል። በነገራችን ላይ ቤቱ ወይም ቢሮው ፕሪንተር ያለው ሰው ፖርታል ውስጥ ገብቶ የራሱን ፋይዳ መታወቂያ ማተም ይችላል። የተለየ ሚስጢር የለውም።

**አዲስ ዘመን:- ኢትዮጵያ ብሔራዊ መታወቂያን ተግባራዊ ማድረጓ በኢኮኖሚዋ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምን ያህል ነው?**

**አቶ ዮዳሄ:-** የብሔራዊ መታወቂያ በኢኮኖሚ ላይ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች አሉ። እነዚህ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት የብሔራዊ መታወቂያ ተግባራዊ መደረጉ በኢትዮጵያ ላይ የ7 በመቶ ተጨማሪ ዕድገት ለማስመዝገብ ያስችላል። አሁን ኢትዮጵያ 200 ቢሊዮን ዶላር በላይ ዓመታዊ ጂዲፒ ያላት ሀገር ነች። ስለዚህ የዚህን ሰባት በመቶ ተጨማሪ ሀብት ማስገኘት ያስችለናል ማለት ነው።

በኢኮኖሚው ረገድ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከሁሉም በላይ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። በዚህ ረገድ በመንግሥት በኩል ያለው ሲታይ ሁሉንም ዜጎች የፋይዳ መታወቂያ ባለቤት ማድረግ ግብር በሚሰበሰብበት ወቅት ከአንድ በላይ መታወቂያ በመያዝ ይከሰቱ የነበሩ ማጭበርበሮች ይቆማሉ። በተጨማሪ ከፍተኛ ቁጥር ያለው መታወቂያ የሌለው ማህበረሰብ የፋይዳ መታወቂያ ባለቤት መሆኑ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በቀላሉ እንዲያገኝ የሚያስችለው ይሆናል። ለምሳሌ የባንክ አካውንት መክፈት፤ የቴሌኮም ስልክ ሲም ካርዶች ማውጣት እና የመሳሰሉትን ባለማግኘቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የማህበረሰብ ክፍል መደበኛውን የኢኮኖሚ ሥርዓት ሳይቀላቀል ቆይቷል።

ዛሬም ድረስ ጥቂት የማይባሉ የማህበረሰብ ክፍሎች መታወቂያ ባለመያዛቸው የገንዘብ ዝውውር የሚፈጽሙትም ሆነ ገንዘባቸውን እያስቀመጡ ያሉት ተገቢ ባልሆነ መንገድ በየቤታቸው ነው። የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀደም የተካሄደ ጥናት እንደሚያመለክተው እንደ ሀገር የብሔራዊ መታወቂያ መተግበር በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት በር የሚከፍት ይሆናል።

በተጨማሪ የፋይዳ መታወቂያ እንደ ሀገር ማንነትን የሚገልጽ ብቻ በመሆኑ እስካሁን ከነበረው በተሻለ ዜጎች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው መሥራት ላይ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ እየተተገበሩ ያሉት መታወቂያዎች በማንነትና በመልክዓ ምድር የተገደቡ ናቸው። ይህ ደግሞ ዜጎች ከቦታ ቦታ እንደልብ ለመንቀሳቀስ ተግዳሮት የሚፈጥሩ ሆነው ቆይቷል። ለቀጣይ ግን የፋይዳ መታወቂያ የያዘ ማንኛውም ግለሰብ በፈለገበት የሀገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሶ ለመሥራት ማንነቱን በሚገልጸው መታወቂያ ይደርስበት የነበረውን ችግር ያስቀርለታል። በጥቅሉ የፋይዳ መታወቂያ መኖር ራስን ለማንቀሳቀስም ሆነ የተለያዩ መንግሥታዊና የግል አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ለማስገኘት የሚያስችል በመሆኑ ዜጎች ትኩረት በመስጠት በየአቅራቢያቸው ባሉ የመመዝገቢያ ጣቢያዎች በመገኘት ምዝገባውን ሊያከናውን ይገባል።

በተመሳሳይ ወንጀልን በመከላከልም ረገድ የፋይዳ መታወቂያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችል ነው። ወንጀልና የማጭበርበር ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላት አንድም ወንጀሉን በሚፈጽሙበት አልያም ከዛ በኋላ ማንነታቸውን መደበቃቸው አይቀርም። የፋይዳ መታወቂያ ተግባራዊ መሆን በአንድ በኩል ወንጀል ለመሥራት የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች ማንነታቸውን እንዳይደብቁ የሚያደርግ ይሆናል። በሌላ በኩል የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ወንጀል እና የማጭበርበር ተግባራትን ያከናወኑ አካላት እንደ ከዚህ ቀደሙ የተለያዩ ሀሰተኛ መታወቂያዎችን በመያዝ የሚደበቁበት እድል አይኖራቸውም። በኢትዮጵያም ገና ከጅምሩ ይህንን ሊያረጋግጡ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ከአዲስ አበባ እና ከክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች እንዲሁም ከፌዴራል ፖሊስ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አሉ። በተግባርም ፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ መተግበር ከጀመረ በኋላ ከተለያዩ ቦታዎች የቀበሌ መታወቂያ አውጥተው ወንጀል ይሠሩ የነበሩ በርካታ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ለማዋል ተችሏል። ይህ ሲጠናቀቅ ደግሞ በተለይም እንደዚህ ዓይነት የጥፋት ተግባራት በስፋት ለሚስተዋሉባቸው ክልሎችም መፍትሔ መሆኑ አይቀርም።

**አዲስ ዘመን:- ስለነበረን ጊዜ ከልብ እናመሰግናለን።**

**አቶ ዮዳሄ:-** እኔም ስለሰጣችሁን እድል ከልብ አመሰግናለሁ።

# ቋሚ ኮሚቴው በአፈር ማዳበሪያ ስርጭት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራ አሳሰበ

## - አራት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመስኖ ልማት እየተሰራጨ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ግብርና ሚኒስቴር በማዳበሪያ ስርጭት ላይ መዘግየት እንዳይኖር ትኩረት ሰጥቶ እንዲሠራ አሳሰበ።ከአራት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ለመስኖ ልማት እየተሰራጨ መሆኑም ተገልጿል።

የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን ላሌ የግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት የ2017 በጀት ዓመት የስድስት ወር እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ ትናንት ሲካሄድ እንዳሳሰቡት፤ የአፈር ማዳበሪያ የማጓጓዣ ሂደቱ የተሻለ የሚባል ቢሆንም፤ ወደ አርሶ አደሩ ከማሰራጨት አኳያ ጥብቅ ክትትል ሊደረግ ይገባል።

ከማዳበሪያ ስርጭት አንጻር በክልሎች አካባቢ መዘግት እንዳይፈጠር መሥሪያ ቤቱ፤ የስርጭት ሥራው እንደየ አካባቢው የዘር ወቅት ፈጥኖ እንዲደርስ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት ገልጸው፤ ብልሹ አሠራሮችን ከመቆጣጠር እና ከመከላከል አንጻር ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በቅርበት መሥራት ይገባልም ብለዋል።

አቶ ሰለሞን እንደተናገሩት፤ ከግብርና ምርምር ተቋማት ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች የገቢ ግብር ክፈሉ የማለትና ከቦታ ጋር ተያይዞም ችግር መኖሩን ቋሚ ኮሚቴው በመስክ ምልከታ አስተውሏል።

በዚህም አንድ የመንግሥት ተቋም ለትርፍ ካልተቋቋመ ግብር እንደማይከፍል በሕግ መቀመጡን የጠቆሙት ሰብሳቢው፤ የምርምር ተቋማት ከሌሉ ግብርናን ማዘመንም ሆነ ማስቀጠል ስለማይቻል ክልሎች የተቋሙን ሥራ እንዳያስተጓጉሉ ትኩረት ተደርጎ መስተካከል እንዳለበት ገልጸዋል።

ሰብሳቢው ከግብርና ምርምር ጋር አያይዘው እንደገለጹት፤ በሦስት ዓመት ውስጥ 175 ከፍተኛ ተመራማሪዎች ሥራ ለቀዋል። የግብርና ምርምር እንዲኖር ከተፈለገ በቂ ተመራማሪ ሊኖር ይገባል። በዚህ ረገድ ከደመወዝ እና ከሌሎች ማበረታቻዎች አንጻር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እንዲሠራ ጠቁመዋል።

አሲዳማ መሬት ለማከም የኖራ መፍጫ ማሽኖችን ተደራሽ ለማድረግ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመቀራረብ ለመሥራት ጥረት መደረግ አለበት ያሉት አቶ ሰለሞን፤ የህብረት ሥራ ማህበራትን ከማጠናከር እና የሻይ ምርትን በማሳደግ ዙሪያም ትኩረት እንዲሰጥ ገልጸዋል።

ሰብሳቢው እንዳሉት፤ በየዓመቱ የማሳ ሽፋን መጨመሩ፤ ከምርት አንጻርም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በአነስተኛ እርሻ 33 ሚሊዮን ኩንታል ጭማሪ ማሳየቱ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው።

በተጨማሪም ምርታማ የሆነ ቡና ምርት ሽፋን ከተመሳሳይ ወቅት አንጻር 164 ሺህ ሄክታር መሬት እድገት ማሳየቱን፤ በሌማት ትሩፋት የወተት ምርት ከተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን እድገት ማሳየቱን በመግለጽ፤ በዶሮ፣ በእንቁላል እና በሌሎች ምርቶች የታየውን እድገት አድንቀዋል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ለ2017/18 የምርት ዘመን ለአፈር ማዳበሪያ አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ዶላር የተመደበ ሲሆን፤ 24 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመግዛት እቅድ ተይዟል።

በምርት ዘመኑ ለመግዛት ከታቀደው የአፈር ማዳበሪያ 13 ሚሊዮን ኩንታል ግዥ ትእዛዝ ተሰጥቷል። እስከ ታኅሣሥ 30 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ኩንታል ማዳበሪያ ወደ ጅቡቲ ወደብ መድረሱን ጠቁመው፤ አንድ ነጥብ 648 ሚሊዮን ኩንታል ወደ ሀገር ውስጥ ተጓጉዟል ብለዋል።

የዓለም አቀፍ ዋጋዎችን በማየት ለመኸር፣ ለመስኖ እና ለበልግ ለየብቻ የአፈር ማዳበሪያ እንደሚገዛ በመግለጽ፤ ከባለፈው ዓመት የተረፈውን እና ዘንድሮ የገባውን ጨምሮ በአጠቃላይ አራት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለመስኖ ልማት መኖሩን ገልጸዋል።

# የዲጂታል ሥርዓት ለዘመኑ ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**



ተክቶ አልያም ደግሞ የተወሰነ የሰው ኃይል ተጠቅሞ ምርት ለማምረትና አገልግሎት ለመስጠት እንዲውል ሲደረግ መሆኑን ይገልጻሉ። ይህም አንደኛ ቀደም ሲል ብዙ የሰው ኃይል የሚያስፈልገው መጠነኛ በሆነ የሰው ጉልበት እንዲመረት የሚያደርግ ሲሆን፤ ሁለተኛ ደግሞ የበለጠ በተስተካከለ፣ ምቹ በሆነና ጥራት ባለው መንገድ ሥራዎች እንዲሠራ ያደርጋል፤ የሥራ ቅልጥፍናን ይጨምራል ሲሉ ይገልጻሉ።

ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ብዙ ስህተቶች በመቀነስ የሰው ጉልበት፣ ግብዓትና የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል የሚሉት ብርሃኑ (ዶ/ር)፤ ይህም ቁጠባን ያመጣል ፣ ብክነትን ይቀንሳል፣ ምርትና ምርታማነት ያሳደጋል ይላሉ።

ምርታማነት ሲያድግ ደግሞ ሀብት የሚጨምርና እድገት የሚያመጣ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሰዎች የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲልና የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ የሚያስችል መሆኑን ያብራራሉ።

ቴክኖሎጂውን ለምርትና ምርታማነት ላይ ስናውለውና ለእድገት ስንጠቀም በብዙ መልኩ የሰዎችን ሕይወት የሚያስተካክል ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል። በተለይ በሕክምና ዘርፍ በቀዶ ህክምናና በከፍተኛ ሁኔታ እጅግ በጣም ፈጣንና ረቂቅ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ በትምህርት ዘርፍ ብዙ አይነት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይገልጻሉ።

አንዱ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆነው ዲጂታል ለሁሉም ዘርፈ ብዙ በሚባል ደረጃ የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሆነ ያመላክታሉ። ‹‹ቴክኖሎጂን ለምርታማነት፣ ለትምህርት፣ ለሕክምና፣ ለግንኙነት እና ለመሰሉ ነገሮች ስንጠቀም ብዙ ጥቅሞችን እናገኛለን። የቴክኖሎጂ ውጤቶች ዓለምን ወደ አንድ መንደርነት እየቀየሩ የመጡ በመሆናቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ ያስገኛሉ›› ብለዋል።

ሌለኛው የምጣኑ ሀብት ባለሙያ አቶ አማኑኤል ቦጋለ ብርሃኑ (ዶ/ር) ከላይ ባነሱት ሃሳብ ይስማማሉ። ቴክኖሎጂ ዓለምን በማስተሳሰር ወደ አንድ መንደር እያመጣ ከመሆኑም በላይ ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝ መሆኑን ያነሳሉ። ቴክኖሎጂ አደገ ማለት ኢኮኖሚውም በዚያው ልክ እንዲያድግ መሠረት የሚጥል መሆኑን ይገልጻሉ።

በተለይ በዚህ ዘመን ከቴክኖሎጂ ውጪ መሆን የማይታሰብበት ጊዜ ላይ እንደመሆናችን ለኢኮኖሚ እድገት ከዘመኑ ጋር አብሮ ለመጓዝ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም በእጅጉ እንደሚያስፈልግ ያመላክታሉ።

ብርሃኑ (ዶ/ር) እንደ ዲጂታል ባንኪንግና ቴሌ ብር የመሳሳሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የአካል ንክኪ ሳይኖር በአጭር ጊዜ የሚደረጉ የኢኮኖሚ ልውውጦችን ፈጣን በሆነ ሁኔታ እንዲካሄድ የሚያስችሉ መሆናቸውን አንስተዋል። ይህም ጊዜንና ወጪን ይቆጥባል፤ በሰዎች የሚፈጸሙ ስህተቶችን በማስተካከል ጥሩውን ነገር ከመጥፎ ለመለየትና ክትትል ለማድረግ የሚረዳ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ዲጂታል ኢኮኖሚ የምንለው በተለያየ በቴክኖሎጂ ውጤት ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ብዙ ጊዜ፣ ጉልበትና ወጪ ሊጠይቅ የሚችለውን የገንዘብ ዝውውር አሁን ላይ በቴሌ ብር፣ ዲጂታል ባንኪንግና በመሰል ቴክኖሎጂ ውጤቶች ቦታ ሳይገድበው በቀላሉ በሰኮንዶች ማስተላለፍ የሚቻልበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ። ገንዘብ ብቻ ሳይሆን መልዕክትንም ሆነ ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ለመላላክና ለመቀባበል የሚቻልበት መሆኑ ለኢኮኖሚው እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይጠቁማሉ።

ኢኮኖሚው አደገ የሚባለው የሚመረተው ምርት ከፍተኛ ሲሆን የሰዎች ገቢና የኑሮ ሁኔታ ሲሻሻል መሆኑን የሚገልጹት ብርሃኑ (ዶ/ር)፤ እነዚህ ጉዳዮችን በአጭር ጊዜ ፣ወጪን በሚቆጥብና በጣም በተቀላጠፈ ሁኔታ በማካሄድ ምርት በማሳደግ፣ ግንኙነትን በማሳለጥ ገንዘብን በማስተላለፍ፣ ግብይትን ማፋጠን ስለሚያስችል ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር በማድረግ ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

አቶ አማኑኤል በበኩላቸው የቴክኖሎጂ ሥራዎች ከጊዜ፣ ከወጪና ከጉልበት አንጻር በአጭር ጊዜ በቀላሉ መሥራት የሚያስችል በመሆኑ ምርታማነትን በእጅጉ የሚጨምር እንደሆነ ይናገራሉ። ምርታማነት ሲጨምር ደግሞ የኢኮኖሚ እድገት የሚያመጣ መሆኑን ያመላክታሉ።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቴክኖሎጂ ጠቀሜታ የጎላ እንደሆነ ሁሉ ጉዳትም ሊኖረው እንደሚችል መገንዘብ እንደሚያስፈልግ ብርሃኑ ደኑ (ዶ/ር) አንስተዋል። የሳይበር ጥቃት እና መሰል ድርጊቶች ሊፈጸሙ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመው፤ ይህንን ተገንዝቦ መከላከያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበር መከላከል እንደሚቻል ያመላክታሉ።

ብርሃኑ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮንም ስንመለከት አደጉ የሚባሉ ሀገሮች በሙሉ በቴክኖሎጂ ፈጣን እድገት ያመጡ ናቸው።ለአብነት ሲጠቅሱ ቻይና በቴክኖሎጂ በመታገዟ በዓለም ፈጣን እድገት እያሳየች ትገኛለች። በመሆኑም በቴክኖሎጂ ላይ ከፍተኛ የሆነ ምርምር ማካሄድ ፣ የሰለጠነ የሰውን ኃይል ከማፍራት አንጻር ልክ አሁን አምስት ሚሊዮን ዜጎች በኮዲንግ ማሠልጠን እየተደረገ ያለ ጥረት በደንብ ሕዝቡን ማስተማርና ተጠቃሚውን እንዲያውቅ ማድረግ ይጠይቃል።

ዘመኑ ብዙ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ብዙ የኢኮኖሚ ግንኙነት የምናደርግበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማስፋፋት ከፍተኛ የሆነ የቴክኖሎጂ እገዛን እንደሚጠይቅ ይገልጻሉ። ወደኋላ የቀረውን የግብርና ዘርፍ በማዘመን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ማድረስ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ እነዚህን ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ ደረጃ በደረጃ እድገታችንን ማፋጠን ያስፈልጋል ይላሉ።

ቴክኖሎጂው በሚፈለገው ልክ ለማስቀጠል ወጣቱን በትምህርት ማዘጋጀት ክህሎት እንዲዳብር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አመልክተው፤ በከተማ ብቻ ሳይሆን በገጠርም ያሉት በትምህርት፣ በሥልጠና፣ እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙና በሥራ ላይ እንዲያውሉ መደረግ እንዳለበት አስገንዝበዋል።

# “የኢትዮጵያን ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አስከብረው ሀገር ማስቀጠላቸውን አስታውሰው፤ የዛሬው ትውልድ በውስብስብ የዓለም ሁኔታ በመቻቻል፣ በአንድነት፣ በበጎነት በሕገ መንግሥታዊ እና በሕግ የበላይነት መርህ የሀገርን ዘላቂነትና ሉዓላዊ ጥቅም ማረጋገጥ የግድ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በማንስማማባቸው ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ምክክር በማድረግ ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል ያሉት አፈ ጉባኤው፤ ለዚህም ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በጥሩ ሂደት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

እስካሁንም በ10 ክልሎችና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች የአጀንዳ ማሰባሰብና የተሳታፊ ልየታ ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁን ገልጸው፤ኢትዮጵያውያን ለምክክሩ ስኬትና በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር በንቃትና በብስለት እንዲሳተፉም ጠይቀዋል።

የመድረኩ የብሔራዊ መግባባት ታሪካዊ መሠረቶች በኢትዮጵያ፣ በአሁኗ ኢትዮጵያ የብሔራዊ መግባባት ተግዳሮቶች፣ የብሔራዊ መግባባት ሚና በቀጣይ ሀገራዊ ግንባታ ላይ ያተኮሩ የመወያያ አጀንዳዎች ቀርበው ዝርዝር ምክክር እንደሚደረግባቸውም ጠቁመዋል።

በፎረሙ ገለጻ ያደረጉት ጌድዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሀገራዊ አንድነት መገንባት በርካታ ውጣ ውረዶች ያሉበት፣ ጊዜ የሚወስድና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

የሀገራዊ መግባባት አለመኖር የእርስ በርስ ግጭቶችን በመፍጠር ለሀብት ውድመት፣ ኢኮኖሚያዊ ድቀትና ለውጪ ጠላቶች ሴራ ተጋላጭ እንደሚያደርግ አመላክተዋል።

ከታሪክ ስህተትና ጥፋት ለመማር ዝግጁ መሆን፣ ለትውልድ የሚሻገሩ ጉዳዮች ሌሎች ችግሮችን ሳይወልዱ መፍትሔ መስጠትና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የምንማረው ነው ብለዋል።

ሀገራዊ አንድነት መገንባት፣ የተረጋጋ ፖለቲካዊ ሥርዓት ለመገንባትና ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ አቅም ለመገንባት ያስችላል ሲሉም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ያገኘችውን ሀገራዊ ምክክር የማድረግ ዕድል ሁሉም አካላት በአግባቡ መጠቀምና በቁርጠኝነት መጠበቅ እንደሚገባቸው ማሳሰባቸውን ከምክክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

# የዘመን ጥበብ

## በምልሰት ወደ ጥምቀት

ሙሉጌታ ብርሃኑ



«በጥምቀት በዓል ላይ የራያ አካባቢ ባህላዊ ጭፈራዎች በስፋት ይታያሉ»፣

ጥምቀት ዞር ብለው ለተመለከቱት አንዳች ምስል አለው፡፡ ለሚናፍቁት መልክ አለው፡፡ ቀናትን አልፈነው ከተጓዝን በኋላ ድንገት በዓይነ ሕሊናችን ውልፍት እያለ፣ አንዱን ጥምቀት ሦስት አራት ባደረገው ብሎ ያስመኘናል፡፡ የከርሞው ጥምቀት ጥላ ዳናው የማንደርስበት እስኪመስለን፣ ከሚመጣው ይልቅ ያለፍነው ያቃጭልብናል፡፡ ሕጻን ቢሆን አዋቂ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ጥምቀትን ያከበረ ሁሉ ዞሮ የሚናፍቀውና የሚመለከተው ምልሰታዊ ቅኝት አለው። እኔም ቀናቶች ካለፉ በኋላ የኋልዮሽ የጎተተኝ ይሄው ትውስታ ነው፡፡

ካየሁትና ከሰማሁት፣ ከሆነውና መሆን ካለበት የጥምቀት ባሕር ጥቂት የቅኝት አሳ ባሰግር ብዬ አሰብኩ። አንዲት ጀልባ ላይ ቆሜ በአንዲት የብዕር መንጠቆ መረቡን ለመሙላት ባይቻለኝም፤ ከዚህም ከዚያም ጨለፍ እያደረግሁ እንደ ትውስታም እንደትዝብትም ጣል ለማድረግ ነው፡፡

በከተራው ከተርን፡፡ በጥምቀቱም ተጠመቅን፡፡ ሦስት ደማቅ ቀናትን አሳልፈን አሁን በአስተርዮ ማርያም ለመገናኘት ያብቃን ተባብለን ተለያይተናል፡፡ "የዘገሊላ ለት፤ የዘገሊላ ለት፤ ነይልኝ በኔ ሞት! ያስተርዮ ማርያም፤ ያስተርዮ ማርያም፤ እመጣለሁ እኔም" ይለዋል ድምጻዊው። በአብዛኛው የሀገራችን አካባቢዎች ያለው እንዲህ ይሁን እንጂ፤ ለአብነትም እንደ ጋምቤላ ክልል ባሉ አንዳንድ ሥፍራዎች ግን ከእኚህ ሦስት ቀናትም ዘለግ ይላል። እንግዲህ እንደነዚህ ላሉት የዛሬዋ ቀን በድምቀት ወደ ጥምቀት የሚሉበት እንጂ ወደ ምልሰት የሚገቡበት ላይሆን ይችላል፡፡ ጊዜና ቦታው፣ መልክና ሁኔታው ቢለያይም ሁላችንም የማንቀርበት ነገር ቢኖር ግን በምልሰት ወደ ጥምቀት መጓዙን ነው፡፡

በጉዞው መሃል አንዳንዴም እንዲህ አለ፤ ቁልቁለቱን ወርዶ ሽቅብ የኋልዮሽ አንጋጦ ለሚመለከት ጥምቀት ለየቅል ነው፡፡ እሱም አመሉን አይለቅ ዘንድሮም እንዲያው ነበረ። ለአንዳንዱ ሎሚ ለአንዳንዱም እንቧይ መሳይ...አንደኛው ሰሞነኛ ሥራዬም ይኼው ነበር፡፡ ሆነ ብዬም፣ ባጋጣሚውም ሁሉ ሎሚ ከእንቧይ ማሽተት ነበር፡፡ ድንገት ላገኘሁት ከሰላምታው ቀጥሎ ጥያቄዬ "ጥምቀት እንዴት ነበረ?" የሚል ነበር፡፡ "ጥምቀት? ጥምቀት? ማን ነው ጥምቀት?" ያለኝ ቀልደኛ ቢጤም አለ፡፡ በቀልዱ ግን ያባው የሆዱን ነው፡፡ በኋላ ላይ በጥምቀት ሳይሆን በጭንቀት ማሳለፉን ነገረኝ። ምክንያቱ ደግሞ፤ ይህ ሰው የነበረበት አካባቢ በሰላም እጦት ከሚናጡት በአንደኛው ስለነበር ነው፡፡ በሁሉም ልብ ውስጥ ውጥረት የነገሠበት እንደነበር አጫወተኝ፡፡ ለጥምቀት ክብረ በዓል በማለት ከወትሮው በተለየ ሁኔታ መንግሥታዊና ማኅበረሰባዊ ዝግጅቶች የተደረጉ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ፍርሃታችን በገዛ አዕምሯችን ላይ ሸብር ይነዛል፡፡ አሁናዊውን ከመመልከት ይልቅ፣ የትናንትናውን 'ሃይላይት' መድገም ወይንም ምልሰታዊ ቅኝት ይማርከናል። "አንድ ነገር የተፈጠረ እንደሆን... እባክህን ልጄ!" በሚለው የእናቱ ተማጽኖ እምብዛም አለማክበሩን ነገረኝ፡፡ ስንቱን አዳዲስ ቅኝታዊ ትውስታዎቹን ያጋራኛል ያልኩት ሰውም እንቧይ መሳይ የነበረ ስለመሆኑ አረዳኝ፡፡ የእርሱ እንዲህ ያለው ቢሆንም በከተማዋ የነበረው የጥምቀት ድምቀትና አከባበሩ ግን መዓዛው የሎሚ ሽታ እንደነበር ሲነግረኝ በቁጭት ክንብንብ ውስጥ ሆኖ ነበር፡፡

የኔውን ውል አልባ የጥምቀት መሰንቆ ትቼ የሌላውን መገዝገዙን ተያይዤው ነበርና ቀሪውን ትቼ በዘንድሮው ዓመት ከጎንደር በተጨማሪ፣ በተለየ ሁኔታ በደማቁ ይከበርባታል ተብሎ በይፉ ስለተነገረላት አካባቢ ልመርቅላችሁ፡፡ ከረዥም ጊዜያት በኋላ ለዚሁ ጣጣዬ የስልክ ጥሪ ያደረግሁለት አንዱ ወዳጄ፣ በትግልም ቢሆን በስተመጨረሻ ሃሎ! ብሎኝ ልናወራ ቻልን፡፡ ካስከተልኩለት ጥያቄዎች አንዱ "እንደተባለውም የዘንድሮው ከሌላው ዓመት ሁሉ የተለየ ሆኖ አገኘኸው?" የሚል ነበር፡፡ "ቃሉ ከገለጸው አዎን የተለየ ነበር ልበል፡፡ እውነቱን ለመናገር በእድሜዬ፣ እኔ ባየሁት እንዲህ ያለው ጥምቀት ተከብሮ አያውቅም፡፡ ...በጎን የመኪና ውድድሩ ትላለህ የብስክሌቱ ከምልህ በላይ ደማቅ ነበር፡፡ በባቱ ደምበል ሐይቅ ላይ የነበረው የጀልባ ትርኢት ደግሞ ከሁሉም ይለያል። በከተራው ዕለት ሐይቁ ላይ 250 ጀልባዎች ናቸው የነበሩት። በዚያ ላይ...የአሏህ!" አለኝ ወዳጄ ሙሲልም ነው፡፡ ታዲያ አሁን የት ነህ? ስል ጠየቅሁት፡፡ "ባሕረ ጥምቀቱ ጋር፡፡ ባንጠመቅም በደንብ አስከባሪነት ሌሎችም አብረውኝ አሉ። የዝዋይ ልጆች እኮ ነን! አይግረምህ!" ብሎ ጥቂት በቀልድ ሊኩራራብኝ ቃጣው። ይህን ተግባሩን ከዚህ ቀደምም የማውቀው ቢሆንም፤ ከዘንድሮው አከባበር ጋር እንዲህ ያለውም ኢትዮጵያዊነት አለ ለማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ከፊት አስቀድሞ ይህን መሳይ አብሮነቶች ከየቦታው አደባባይ ይወጣሉ፡፡ ዳሩ ዛሬ ዛሬ ብርቃችን ሆኖ እንጂ፤ መስጂድ የሚያስገነባ ቄስ፣ ቤተ ክርስቲያን የሚያሳንጽ ሸህ የነበረባት ሀገር እኮ ናት፡፡

**አንቺ እዚያ ማዶ፤**
**እኔ እዚህ ማዶ፤**
**ሀሳቤ ካንቺ ጋር፤**
**የሩቅ አንቺን ወዶ፡፡**

እንደኔው ያላት አይጠፋ ይሆናል፡፡ እንደኔው ከዘንድሮው መዓዛዋ ውልብ እንዲልበት የተመኘም ብዙው እንደሆን ያለነጋሪም ይሰማኛል፡፡ ቁልቁለቱ ላይ ሆኜ ሽቅብ ለመመልከት ባልችል፣ ቁልቁል ለመስማት የወሬ ነጋሪውን ወሬ በጉጉት ከጠበቅኳቸው አንዷ የእናትዋ ጎንደርን የጥቅምት ውሎ አዳር ነበር፡፡ ከዓለም ጫፍ እስከ ጫፍ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብና ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሀገራችን እያንዳንዱ አካባቢ ተነስቶ በጥምቀት ጎንደርን ለመርገጥ የሚተመው፣ ለወትሮው ቁጥር ስፍር የሌለው ሕዝብ ነበር። በእርግጥ ከአምናው ቢሻልም፣ የዘንድሮውን ከዓመታት በፊት በምናውቅላት ልክ ነበር ለማለት አያስደፍርም፡፡ አስቀድሞም ይሆናል ብሎ የሚጠብቅ እንደማይኖር ግልጽ ነው፡፡

ይሁንና የከተማ አስተዳደሩ አስቀድሞ ባወጣው መግለጫው ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ዝግጅቷን አጠናቃ፣ ጎንደር ሽር ብትን በማለት ላይ እንደሆነች አስታውቆ ነበር፡፡ ለዚህም ይመስላል የአፄ ፋሲለደስ ቤተ መንግሥት በአጭር ጊዜ ውስጥ በተዋበ እድሳት ማሸብረቁ፡፡ በአዳዲስ ኩሎቿ ተኩላ ለመሞሸር ትጠብቅ የነበረው አጃቢዎቿን ነበር፡፡ ከቀናት በፊት ደግሞ የመይሳዎቹ የፋሲል ከነማ ደጋፊዎች ከተማዋን የጥምቀት ጃኖ አስመስለዋት ነበር፡፡ ሙሽራይቱ ጎንደር ታዲያ ካባዋ የሚያንጸባርቀው በኮቴ ግርግር ብቻ አይደለምና የወጉን አድርሳ፣ ወጓን ማየቷ አልቀረም። የተንጣለለው የጃንተከል ዋርካ ብዙውን እንግዳ እቅፍ አድርጎ ከጉያው አድርጓል። በኪነ ሕንጻ ጥበብ ደረታቸውን ሰጥተው በግርማ ሞገስ የቆሙት ቤተ መንግሥቶች ፍቅር የተሞላበትን አስተየታቸውን ቸረዋል፡፡ ደጋጎቹ የጎንደር ልጆች የመጣውን ሁሉ በክብር እየተቀበሉ አሰናብተውታል። አርባ አራቱ ታቦታት ወጥተው እልል! ለሀገሬ እያስባሉ ሁሉን አንድ አድርገው ሰንብተዋል፡፡

ወግድ!... የምን ወዲያ ወዲህ! ከእናትዋ ጎንደር፣ ከናታለም ተራራ እምር ብሎ፣ ጥምቀትን በቁልቁለቷ ሲወርድ ያጀበው የናፍቆት እንባ ነው፡፡

**"ዓመት ድገመኝ ጌታዬ**
**ከርሞስ ብትደግም እኔ ምንተዳዬ፡፡"**

እያለ የከርሞውንም ዘንድሮ እንዲደግምለት በዜማው ሲማጸን ነበር አሉ፡፡ ድሮስ ጥምቀት ያለ ጎንደር፣ ጎንደር ያለ ጥምቀት እንደምን አፍታ እስትንፋስ ሊኖራቸው? የዘንድሮውን የጥምቀት ድባብ እንደ ሀገር ጠቅለል ካደረግነው፣ ከጎንደር በተጨማሪ በባቱና በኢራንቡቲም በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

ምን ቢሆን በጥምቀት፣ ማን ቢሄድ ለጥምቀት...አዲስ አበባም የብቸኝነት ጥንቅሽ እየበላች ብቻዋን አትቀርም፡፡

**ባዲስ አበባማ፤**
**አዲስ አበባማ፤**
**ጥምቀቱ ድማማ!**

እንደልማዷ፣ እንዳስለመደችንና እንደለመደችው ሁሉ ዘንድሮም ወገቧ አልጎበጠም፤ ትከሻዋም አልዛለም። "እንጨዋወት ተጨዋወቱ፤ ባገሬ ወግ አግባብ፤ እንበል እንዋብ...የሀገሬን ትዝታ፤ በባሕል ጨዋታ..." ስትል ሰነባብታለች፡፡ ጥምቀት አንድ ከሃይማኖት፣ አንድ ከባሕል ሜዳ ነው፡፡ ሜዳ ካሉ ደግሞ አንደኛው ጃንሜዳ ነው፡፡ አዲስ አበቤው ከጃን ሜዳ ከትሞ፣ ጥምቀትን ከአቦል እስከ ማክተሚያው ፉት! ሲል ነበር፡፡

ሰው ሁሉ አምሮና ደምቆ ከጥምቀተ ባሕሩ እየወጣ በደስታና ጨዋታ ጮቤ ሲረግጥ ነበር፡፡ መቼም የዘንድሮ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ደግሞ ለዚህ ያመቹ ነበሩ፡፡ በኮሪደር ልማቱ የሰፋውን ወገብ፣ በጥምቀት ሻሽ አስረው ሲደልቁበት "አቤት ማማሩ!" የሚያሰኝ ነበር፡፡ በተለይ በጥምቀት አመሻሽ መላው የአዲስ አበባ አውራ ጎዳናዎች በከበሮ ታጅበው ድቤ ከጮቤ ተረግጦባቸዋል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ገና በጅምር ያለው አቧራ እየጨሰ ዓመድ ቢነሰንስም፣ ነጻነቱ ግን ለታቦታቱም ያመቹ ነበር፡፡ ሁሉም "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ!" እያለ የሚወጣ በመሆኑ አቧራውም ቢሆን "አቧራው ጨሰ!" ሲባልበት እየቦነነ ከዓይን ከመግባቱ ይልቅ፣ እየጨሰ ጨዋታ ማድራቱ ይበልጣል፡፡ እንዲህ ባሉ ቅጽበቶች ብዙ የማንወዳቸው ነገሮች ሁሉ ይበልጥ ልባችንን የሚያሞቁ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በእስክስታ እየተወረገረጉ ከሰውነት ላይ ቁልቁል የሚፍለቀለቀው ላበት በራሱ አንዳች የሚሰጥ ልዩ ስሜት አለው፡፡ ያለንን አቅም ሁሉ አሟጠን መጫወታችንን ስናስበው፣ ለጥምቀት ያልሆነ...ያልነውን ቃል እንደፈጸምን ሁሉ ደስታውንም ከልብ ያፈልቃል፡፡ ሰው ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮም አብሮ ለመገማሸር ያሰኘው ይመስል ነበር፡፡

**"ኸረ አዘቀዘቀች ፀሐይ**
**የቆንጆዎቹን አንገት ልታይ፡፡"**

ሲሉ ሎሚ ብርሃኗን ይዛ ለወጣች ፀሐይም በዜማዎቻቸው ሲያጨዋውቷት ነበር፡፡ በጥምቀት ማልዳ የወጣች ፀሐይም፤ ጠዋቱን ሞቅ አድርጋ ቀትር ከነበልባልዋ መልስ እየተባረደች፣ ከሰዓቱን ሲረፋፍድ አጫፍራ ጥልቅ አለች፡፡ ጨረቃም ምሽቱን አደማምቃ ወዝ ወዝ እያለች፣ እሷም እንደልማዷ ንጋት እልም ማለቷ አልቀረም። ከሁለቱም ጋር አብሮ፣ ሁለቱንም ሲያውረገርግ የነበረው "ዘገሊላ" ግን ከሰሞኑ መድረኩን አለቅ ብሎ ብሶበት ታይቷል። ተደምጧል። የገና በዓል ከተራራው እየወረደ ለመሄድ ቁልቁለቱን ሲያያዝ ገና፣ የይሁኔ በላይ "ዘገሊላ" ከታች ሽቅብ ተራራውን እየወጣ ድምጹ ከፍ ብሎ መደመጥ ይጀምራል። ይሄው የዘንድሮውንም ጥምቀት አንድ እሱ ብቻ ያለ እስኪመስል ድረስ የአዲስ አበባን ሳሎንና ጓዳ፣ የወጪና ወራጁን ጆሮ እንደተቆጣጠረ ሰንብቷል። ከአምናው ዘንድሮ ብሶ ብመለከተው ጊዜ፣ ምናልባትም የ21ኛውን ዓመት የልደት በዓሉን በማስመልከት ይሆን እንዴ? ስል አሰብኩኝ። ጥምቀትን ብቻ ሳይሆን የራሱንም በማክበር ላይ ስለመሆኑ እርግጠኛ ባልሆንም፣ በዘንድሮው 21ኛው ዓመቱ በልዩነት ስለመደመጡ ግን በበኩሌ አልተጠራጠርኩም፡፡

ያለፈውን ስላልሰሙት ነበር ብለን እንዝለላቸውና በእነዚህ ሀያ አንድ ዓመታት መካከል የዘገሊላን ሙዚቃዊ ቃና አድምጠው የተሠሩ በርካታ ሙዚቃዎች አሉ፡፡ ሁሉም የየራሳቸው የሆነ መዓዛ ቢኖራቸውም፤ በእነዚህ ሁሉ ላይ የነገሠው ግን የይሁኔ በላይ "ዘገሊላ" መሆኑ ግልጽ ነው። በጥምቀት ግዛት ውስጥ ለድፍን 21 ዓመታት ብቻውን ስናነግሠው፣ የሚገዳደረው ታጣ? ወይንስ ከዙፋኑ ለማነቃነቅ ሀፍረትና ይሉኝታ ይዞን? ብዬ አሰብኩ፡፡ እናም በዚህ የጥምቀት ክብረ በዓል ማድመቂያ የሆኑትን አብዛኞዎቹን ሙዚቃዎች ደጋግሜ ለማድመጥ ሞከርኩ፡፡ ቢሆንልኝ ሌላ የጥምቀት እንደራሴ እጩ አቅርቤ፣ ቢልልኝ በዘገሊላ ፈንታ በግሌ እንኳን ለመሾም ነበር፡፡ ግን ሳይሆንልኝ ቀረ። መቼስ ጥበብ የሾመችውን ማንስ ሊያወርደው ይቻለዋል? የነበረኝ ምርጫ፣ ዘገሊላ እውነተኛ የጥምቀት ዓርማ መሆኑን አምኜ መቀበል ነበር፡፡ ከዚህ ወዲያ የነበረኝ አንድ ነገርም፤ ድምጻዊውን ከልብ አመስግኜ፣ እያደነቁት ብቻ ደጋግሞ ማድመጥ ብቻ ነበር፡፡ 21 ታንሳለችና ገና ብዙ የንግሥና ዘመናትን ተመኘሁለት፡፡ ተገዳዳሪው ግን፤ እሱም ጉልበቱ ሳይዝል ከጎን ብቅ እንዲልለት ሌላኛው ምኞቴ ነው፡፡

ምኞቴ እንደምኞቷ ይሁንና ጥምቀትን በምን ታዘብኳት ብትሉኝ፤ ምላሼ በሎሚው የሚል ነው፡፡

**"ሎሚ ብወረውር**
**ደረቱን መታሁት**
**አወይ! ኩላሊቱን**
**ልቡን ባገኘሁት፡፡"** ባለችበት ድምጻዊት፣ ሎሚው ቀርቶ ድምጽዋ ብቻ መቅረቱ አያስተዛዝብም የሚለኝ ካለ በጥምቀት አድባር፣ በባሕረ ጥምቀቱ ሸንጎ ላይ ቆሞ ይሞግተኝ። "በላ! ልበልሃ!" እያለ ጎራ ለይቶ "ስተሃል! ተመለስ!" የሚለኝ ያለ አይመስለኝም፡፡ የምንታዘበው ማንን እንደሆን ባናውቅም፣ በሁላችንም የትዝብት ልብ ውስጥ ያለ ነገር ስለመሆኑ ሀቅ ነው።

ሎሚ በጥምቀት የበዓሉ ማድመቂያ ነው ልንል እንችል ይሆናል፡፡ ዓይን አዋጅ ከሆነበት የቆነጃጅትና ሸጋ ወጣቶች መሃል ለመሃል አንዱን ወይ አንዷን መርጦ፣ በፍቅር ለመተጫጨት ነው ብለንም እናስብ። የጣልነውና የተውነው ግን ባሕልን ነው፡፡ የጥምቀትን ያንገት ላይ ዶቃ ነው፡፡ በዩኔስኮ ካስመዘገብነው የጥምቀት ትውፊታዊ ገጽታ ላይ ሸርፈን ያስቀረነው አንዳች ነገር አለው። ቆርሰን ያጎደልነው ውበት እንዳለም ይሰማኛል፡፡ ድሮ ድሮ እጅግ የተከበረና በርካቶች በቁም ነገር ሕይወታቸውን ያጌጡበት ነበር፡፡ ባሕላቸውን ሳይዘነጉ፣ እሴቱን ቸል ሳይሉ ከዓመት ዓመት በጉጉት የሚጠባበቁት የጥምቀት ትውፊት ሳለ አሁን አሁን ግን ቁም ነገሩ ቀርቶ ለጨዋታው እንኳን አይታይም። አስደናቂው የባሕል ገጽታችን ነው ብለን ለዓለም እስካስተዋወቅን ድረስ አሁንም ከናካቴው ጠፍቶ እኛም ሳንረሳው አንድ መላ ልናበጅለት ይገባል፡፡ ቀድሞ የነበረውን ሙሉ እሴታዊ ወጉን ለመጠበቅ ባንችል፣ ጨዋታዊ ትውፊት እንኳ ብናደርገው አንድ ነገር ነው፡፡ ብንችል እንደቀድሞው በፍቅር በተመኘነው ደረት ቢያርፍ፡፡ እንዲያው ከምንጥለው ግን ለሌላውም፣ እርስ በርስ ፍቅራችንን የምንገልጽበት፣ እንዲሁም "እንኳን አደረሰህ! እንኳን አደረሰሽ!" ተባብለን መልካም ምኞታችንን የምንለዋውጥበት የጥምቀት ስጦታ ብናደርገው፤ በግሌ መልካም ነው ብዬ አሰብኩ፡፡

እንግዲህ ጥምቀትን ከያዙት የበሽሎ ወንዝ የማይስተካከለው፣ ዓባይም ቢሆን እያሶመሶመ የማይደርሰው የአጽናፍ ጉዞ ነው፡፡ ሽቅብ እየወረድን ከአንዷ ቁልቁለት ስር ቆም ብለን ይህቺን ታህል ገርመም ካደረግናት፣ በቂ ባትሆንም ማብቃቱ ግን ምርጫም የለሽ ነው፡፡

**"ከርሞ እንገናኝ ለዓመት**
**አንተም ደህና ብትሆን፣ እኛም ባንሞት"**
**ያላችሁ እንደሆን...**
**"እኔስ ለዚህች ዓለም እሳሳለሁ**
**አምና የነበሩት ሲቀሩ አይቻለሁ፡፡"**

በማለት እንደ ወጉ ከጨዋታው ላይ እኚህን ስንኞች መምዘዜ የማይቀር ነው፡፡ ቁልቁለቱን ጨርሰን ወደ ሜዳው መግባታችን ነውና የከርሞ ሰው ይበለን!!

# ተቋማት መሪዎቻቸውን ይመስላሉ!

**እስማኤል አረቦ**

በሀገራችን ጓደኛህን ንገረኝ እና ማንነትህን እነግረሃለሁ የሚል የቆየ አባባል አለ፡፡ ይህን አባባል በተመሳሳይ መልኩ ተቋማትን ንገረኝ እና መሪዎቻቸውን እነግርሃለሁ በሚል ቢተካ የሚያስኬድ ነው፡፡ መልካም ጓደኛ ያፈራ መልካም ባሕሪ እንደሚወርስ ሁሉ ጠንካራ መሪ ያለውም ተቋም ጠንካራ ውጤት ያመጣል፡፡ በአጠቃላይ ጠንካራ ተቋማት የጠንካራ አመራር ውጤት ነው፡፡

ጥሩ አመራር ተቋም ይወልዳል፡፡ የወደቀውን ያነሳል፤ የደከመውን ያበረታል፤ ለሞት የተቃረበውን ነፍስ ይዘራል፡፡ ጠንካራ መሪዎች ያረጀውን ተቋም እንደንስር ያድሳሉ፤ ወጣት ያደርጋሉ፡፡ በታዘብናቸው አንዳንድ ተቋማትም ያየነው ይህንኑ ነው፡፡ ለዚህ እንደማሳያ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፡፡

የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ሥርዓቱ ጤናማ እንዲሆን እና ለሀገር እድገት አወንታዊ ሚና እንዲጫወት የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ነው፡፡ ይህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከሀገር ውስጥ አልፎም ቀጣናዊ ትስስርን በማጠናከር የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና በኢኮኖሚ እንዲተሳሰር ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም ነው፡፡

ሆኖም ባለፉት ዓመታት የንግድ ሥርዓቱን በሕገወጥ ነጋዴዎች እና ደላሎች ሲዘወር እና ዜጎችም በየዕለቱ በሚያሻቅበው ኑሮ ውድነት ሲሰቃዩ መታደግ ያልቻለ ተቋም መሆኑን ብዙዎች የሚስማሙበት ነው፡፡

ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም የሚተዳደረው በግብርና ነው፡፡ ኢትዮጵያም ከሰሐራ በታች ካሉ ሀገራት በሚታረስ የእርሻ መሬትና በግብርና ምርት ቀዳሚ ሀገር ናት፡፡ ሆኖም በተቃራኒው የግብርና ምርቶችና ሌሎች መሠረታዊ አቅርቦቶች እጥረት ካለባቸውና ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ከሚታይባቸው ሀገራትም አንዷ ሆና ቆይታለች ፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛው የንግድ ሥርዓቱ በአግባቡ ባለመመራቱ የተከሰተ ነው፡፡

በተለይም ኅብረተሰቡ በዕለት ተዕለት በሚጠቀምባቸው መሠረታዊ ፍጆታዎች ላይ ሲታይ የቆየው የዋጋ ንረት ብዙዎችን አማሯል። ሕገወጥ ደላሎች እና ነጋዴዎች እንደልብ ሲፈነጩበት በቆየው የንግድ ሥርዓት ውስጥ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እንደሕዝቡ ከማማረር ውጭ የፈየደው አንዳችም ጉዳይ አልነበረም፡፡ መሸቶ በነጋ ቁጥር «ከገበያ ጠፍተዋል»፤ «ዋጋ ጨምሯል» የሚሉ ሕዝብን የሚያማርሩ ንግግሮች የሕገወጥ ነጋዴዎችን የበላይነት የሚያሳዩ ነበሩ፡፡

እነዚህን እና መሰል ጉዳዮች የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርን ጥርስ የሌለው አንበሳ አድርገውት ቆይተዋል፡፡ ስለዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሕዝብ የተጣለበትን አደራ እንዲወጣ የአመራር ለውጥ ማስፈለጉን ይህ ፀሐፊ የሚስማማበት ጉዳይ ነው። የፀሐፊው ትዝብት ውሃ እንደሚያነሳ ለመገንዘብም ከአመራር ለውጡ በኋላ በገሃድ የታዩ ለውጦች ማሳያዎች ናቸው፡፡

ቀደም ባለው አመራር ከሚታዩ ውስብስብ ችግሮች አንዱ ነዳጅን የተመለከተ ነው፡፡ ነዳጅ ስትራቴጂክ ሸቀጥ ነው፡፡ ስለዚህም ስትራቴጂክ አመራር ያስፈልገዋል። ከዚህ ቀደም በነበረው አመራር ነዳጅ በአግባቡ ባለመመራቱ ሀገር ላይ ከፍተኛ ዕዳ ከመቆለሉም በላይ ኮንትሮባንዲስቶች እና በጎረቤት ሀገራት ጭምር የሚገኙ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ሲከብሩበት ቆይተዋል፡፡

ይህንኑ ችግር የተረዱት አዳዲሶቹ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ኃላፊዎች ዘርፉን ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ በመምራት ከችግሩ እያላቀቁት ይገኛሉ፡፡ የነዳጅ ውጤቶችን ግብይት የሚደነግገ አዋጅ ከማውጣት ጀምሮ በየስርቻው ያሉ ሕገወጦችን እያደኑ እርምጃ እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡ ሰሞኑንም 250 የሚጠጉ ነዳጅ ጭነው በጥሻው ተደብቀው የነበሩ አሽከርካሪዎች ላይ የተወሰደው እርምጃ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ጥንካሬ ያሳየ ነው፡፡

የነዳጅ ውጤቶች ካላቸው ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር ስትራቴጂክ ምርቶች ናቸው። አቅርቦታቸው፣ ክምችታቸው፣ ስርጭታቸው፣ ደኅንነታ ቸው እና ጥራታቸው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆን ይኖርበታል፡፡ አዲሱ አመራርም ይህንኑ በአግባቡ ለመምራት እና በነዳጅ ላይ የሚፈጸሙ ሕገወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል አዋጅ እንዲወጣ አድርጓል፡፡

> **ጠንካራ መሪዎች ያረጀውን ተቋም እንደንስር ያድሳሉ፤ ወጣት ያደርጋሉ፡፡ በታዘብናቸው አንዳንድ ተቋማትም ያየነው ይህንኑ ነው፡፡ ለዚህ እንደማሳያ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው**

አዋጁ በሕገወጦች ላይ እስር እና የገንዘብ ቅጣት ደንግጓል፡፡ በሕገ-ወጥ የነዳጅ ግብይት ላይ የተጣለው የእስር እና የገንዘብ ቅጣት በሀገር እና በሕዝብ ሀብት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን የሚታደግ ነው፡፡ ከነዳጅ አስመጪዎች ጀምሮ እስከታችኛው ተጠቃሚ ድረስ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ አስተማማኝ፣ ፍትሐዊ እና ተደራሽ የአቅርቦት፣ የስርጭትና የችርቻሮ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት የሚያስችል ነው፡፡

በነዳጅ ውጤቶች የግብይት ሰንሰለቶች ውስጥ እየታዩ ያሉ ሕገ-ወጥ ተግዳሮቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ምቹ ሁኔታንም የሚፈጥር ነው፡፡ ነዳጅ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገዛ፤ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ የግብይት ሥርዓቱ በጥንቃቄና በአግባቡ ሊመራ የሚገባው ነው፡፡

በአዋጁ የተጣሉ ድንጋጌዎችም ነዳጅ እያለ ሆነ ብሎ ገበያውን ለማወክና ለግል ጥቅም ሲባል ነዳጅ የለም የሚሉ ማደያዎች እና ነዳጅን በኮንትሮባንድ የሚነግዱ አካላትን አደብ የሚያስገዛ ነው፡፡ አዋጁ ከወጣም በኋላ የታየው ለውጥም በእጅጉ የሚያስመሰግን እና በቀጣይም ነዳጅን አስታኮ በሕገወጥ መንገድ ለመክበር የሚደረገው ውጣወረድ የመከነ እንደሆነ ከወዲሁ መመስከር ይቻላል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነውም በሕገወጥ ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ግለሰቦችን ለመቅጣት የተደረገው አስተማሪ እርምጃ ነው፡፡ ነዳጅ በሕገ-ወጥ መንገድ በማጓጓዝ የተሳተፉ ኩባንያዎች 116 ሚሊዮን ብር እንዲቀጡ ለማድረግ ከመቻሉም በላይ ባለፉት 6 ወራት የነዳጅ ግብይትን ሥርዓት ለማስያዝ በተሠራ ሥራ በሕገ-ወጥ መንገድ ሲጓጓዝ የነበረ 325 ሺህ ሊትር ነዳጅ በቁጥጥር ስር መዋሉን ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

አዋጁ በአጠቃላይ በነዳጅ ግብይት ላይ የሚታየውን ሕገ-ወጥ ግብይት ሥርዓት ለማስያዝ የሚረዳ፣ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን እና አሠራሮችንም የሚያዘምን ነው፡፡ እያንዳንዱ ማደያ ምን ያህል ነዳጅ አለው? እንዴት ዓይነት አገልግሎት እየሰጠ ነው? የሚለውንም ጭምር ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ከኢትዮ ቴሌኮምና ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር በመተባበር የግብይት ሥርዓቱን ለማስተካከል የሚሠራበት የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ካስመዘገባቸው ለውጦች መካከል ሌላኛው ተጠቃሽ ጉዳይ በሲሚንቶ ግብይት ላይ የታየው አወንታዊ ለውጥ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በነበረው አሠራር ሲሚንቶ በከፍተኛ ሁኔታ ለኮንትሮባንድ የተጋለጠ እና ኅብረተሰቡም በዚህ ጉዳይ ምሬት ሲያሰማ እንደቆየ የሚታወቅ ነው። ከፍላጎት፣ መጨመር ጋር ተያይዞ ደላላዎች፤ አምራቾች እና አከፋፋዮች በሚፈጥሩት አሻጥር በየቀኑ የሲሚንቶ ዋጋ ሲጨምር ቆይቷል፡፡ ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ ከሰኔ 17 ቀን 2014 ጀምሮ ተግባር ላይ የዋለ የሲሚንቶ ግብይትና ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 908/2014 ቢወጣም በአግባቡ ባለመሠራቱ ሲሚንቶ ለኮንትሮባንድ እና ብልሹ አሠራር የተጋለጠ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ሆኖም በቅርቡ በተደረጉ ለውጦች እና የአመራር ጥበቦች የሲሚንቶ ዋጋ ከመቀነሱም ባሻገር ኮንትሮባንድ እና ብልሹ አሠራሮች በእጅጉ ቀንሰው ታይተዋል። በሲሚንቶ ግብይት ማሻሻያ የተረጋጋ አቅርቦትና ግብይት እንዲኖር በመደረጉ ዋጋው በግማሽ መቀነሱንም ሚኒስትሩ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባጋሩት ጽሑፍ ጠቅሰዋል። በጨው ግብይት ሪፎርምም በጥቂት ነጋዴዎች በሞኖፖል ተይዞ የነበረው ግብይት በፍትሐዊነት ለሁሉም ክፍት መደረጉን ጠቁመዋል፡፡

ከእነዚህ ተጨባጭ ለውጦች በተጨማሪ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሕገወጥ ኬላዎችን በተመለከተ የያዘው አቋም ሊሰመርበት የሚገባው ነው፡፡ ሕግ ማክበር የሥልጣኔዎች ሁሉ መጀመሪያ ነው፡፡ አንድ ማኅበረሰብ ሠለጠነ፤ አደገ የሚባለው ሕግና ሥርዓትን ማክበር ሲችል ነው፡፡ ሕግና ሥርዓት እንዲከበር ጥረት የማያደርግ አስተዳደርና ማኅበረሰብ ለግጭት፤ ሁከትና አለመረጋጋት ይዳርጋል፡፡ በልማት ወደ ኋላ ይቀራል፤ በኑሮ ውድነት ይሰቃያል፤ ድህነትና ጉስቁልና መለያው ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የመንግሥት ሥርዓት ያላትና ዜጎችም በሕግና በሥርዓት መተዳደር ልማድ ያደረጉ ሕዝቦች መኖሪያ ናት፡፡ በርካታ የዓለም ሀገራት የመንግሥት ሥርዓት ባለቤት ሳይሆኑ በፊት ኢትዮጵያ ሕግና ሥርዓት ባለው መልኩ የመተዳደር ባሕል ያለው ሥልጡን ሕዝብ ያለባት ሀገር ነች፡፡ በጥንታዊ የገባር ሥርዓት ሳይቀር መንግሥት ተገቢውን ግብር እየሰበሰበ የሀገርን አንድነትና ሉዓላዊነት ሲያስጠብቅ ኖሯል። ለዘመናትም በጸናው የኢትዮጵያ የመንግሥት ታሪክ ኬላዎችን ጨምሮ ግብር መሰብሰብ የመንግሥት ብቸኛ መብትና ኃላፊነት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ኬላዎችን የመክፈትና የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቢሆንም በየስርቻው በጎበዝ አለቆች የሚመሩ ኬላዎች ተበራክተዋል፡፡ እነዚህ ኬላዎች እንዳሻቸው በሸቀጦች ላይ የዋጋ ትመና ከማድረጋቸው ባለፈ የግብርና ምርቶች ወደ ተጠቃሚው እንዳይደርስ እንቅፋት እየሆኑ ነው፡፡ ይህም ለሸቀጦች ዋጋ መጨመርና ለኑሮ ውድነቱ መንስኤ እየሆነ ከመምጣቱም ባሻገር እንደሀገር አለመረጋጋትን የሚፈጥር ነው፡፡

ሕገወጥ ኬላዎች የሕገወጥ መሣሪያ፤ የአደንዛዥ ዕፅ፤ የሕገወጥ ለሰዎች እና የኮትሮባንድ ዕቃዎች ዝውውር ዋነኛ መተላለፊያዎች ከመሆናቸውም ባሻገር ሽፍቶችና የሰፈር አለቆች እንዲበራከቱ በማድረግ ኅብረተሰቡ በመንግሥት ላይ ያለውን እምነት የሚሸረሽር ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ራሳቸውን እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ በሚቆጥሩ ግለሰቦችና ቡድኖች አማካኝነት ሕጋዊ ነጋዴዎችን አላስፈላጊ ገንዘብ በመጠየቅና ለእንግልትና ውጣውረድ በመዳረግ ላይ መሆናቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሀሳባቸውን የሰጡ ግለሰቦች ያስረዳሉ፡፡ በተለይም እነዚህ ሕገወጥ ሰዎች በየቦታው ባቋቋሟቸው ሕገወጥ ኬላዎች አማካኝነት የግብርና እህል የጫኑ ተሽከርካሪዎች ለተደራራቢ ቀረጥ በመዳረጋቸው ምክንያት የግብርና ምርቶች ላልተገባ የዋጋ ጭማሪ ተዳርገዋል፡፡

በየኬላው የሚፈጸመው ሕገወጥ ቀረጥም የግብርና ምርቶች ወደ ተጠቃሚው በቀላሉ እንዳይደርስ እንቅፋት ከመሆኑም ባሻገር በተለይ በከተሞች አካባቢ የዋጋ ንረት እንዲባባስ ምክንያት እየሆኑ መጥተዋል፡፡

የፌዴራል መንግሥት በሚስተዳድራቸው ነባር ኬላዎች ጭምር እነዚህ ሕገወጥ ግለሰቦችና ቡድኖች በሚፈጽሟቸው ተግባራት ምክንያት የሰብዓዊ ርዳታዎች ጭምር ለተረጂዎች በቀላሉ ማድረስ አዳጋች ሆኗል። ከዚህም ባለፈ ሕገመንግሥታዊ የሆነው የሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋውሮ የመሥራት መብትንም የገደበ እስከ መሆን ደርሷል፡፡

የአንድ ቅቡልነት መንግሥት መለያ ከሆኑት ውስጥ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ኬላዎችን በአግባቡ ማስተዳደርና ኅብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል ነውና ኬላዎችን ከሰፈር አለቆች ነፃ ማድረግ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። በቅርቡ አንድ የከባድ ተሽከርካሪ ሾፌር ሲናገሩ እንደተደመጡት ከጅቡቲ አዲስ አበባ እስኪደርሱ ድረስ 12 ቦታዎች ላይ በሕገወጥ መንገድ ተቀርጠዋል፡፡ ይህ እንግዲህ ጎበዝ አለቆች ምን ያህል በማንአለብኝነት ኬላዎችን የግል መጠቀሚያቸው እያደረጓቸው እንደመጡ ማሳያ ነው፡፡

በአጠቃላይ በኬላዎች ላይ የሚታዩት ሕገወጥ ተግባራት ከግብርና ምርቶች ማሻቀብ በተጨማሪ ለሕገወጥ መሣሪያ፤ ለአደንዛዥ ዕፅና ለሕገወጥ ሰዎች የሚዳርግና ኮንትሮባንድንም በከፍተኛ ሁኔታ የሚያስፋፋ በመሆኑ መንግሥት ተገቢውን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ጉዳዩ የሰዎችንም ተዘዋውሮ የመሥራት መብትን የሚገድብና በየቦታው ተፈናቅለው ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሰብዓዊ ድጋፎችንም ለማቅረብ እንቅፋት እየሆነ ስለሚገኝ መንግሥት የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድቶ ሕገወጦችን ሥርዓት ሊያሲዛቸው ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሕገወጥ ኬላዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርገው ውትወታ ሊደመጥ ይገባል፡፡

የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር መሥሪያ ቤት ጥንካሬ ሕገወጥ አካሄዶችን መስመር ከማስያዝ በተጨማሪ የውጭ ንግዱ እመርታዊ ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል። ባለፉት ስድስት ወራት ከወጪ ንግድ ከሦስት ነጥብ 28 ቢሊዮን ዶላር በላይ በማግኘት ሀገሪቱ አዲስ ታሪክ መጻፍ ችሏል፡፡ አምና እና ካቻምና ይህ የገንዘብ መጠን የሀገሪቱ ዓመታዊ የወጪ ንግድ ገቢ መሆኑንም ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# የተፋሰስ ልማት ሥራው -...

**ከገጽ 5 የዞረ**

ይሄም በኢትዮጵያ ያሉትን የተፈጥሮ ሀብት ፀጋዎች በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ ለሀገሪቱ እድገት ጉልህ ሚና እንዲያበረክቱ ማድረግ፤ ካልሆነ ግን እውነታው በተቃራኒው እንደሚሆን ማሳያ ነው:: ለአብነትም፣ የኢትዮጵያ የደን ሀብት ከነበረበት 40 በመቶ ሽፋን ወደ ሁለት ነጥብ ሰባት በመቶ ደርሶ የአፈር ሀብቱ ሳይቀር በጎርፍ እየተጠረገ ወደ ጎረቤት ሀገሮች የሚጋዝበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር::

ሆኖም በተፈጥሮ ሀብት ላይ የተጋረጠውን ችግር ለመቅረፍ መንግሥት አበክሮ በመሥራቱ ዛሬ ላይ ችግሩን መቀልበስ ወደሚቻልበት ደረጃ ላይ ማድረስ፤ የደን ሽፋኑንም ማሳደግ ተችሏል:: ይሄን ከማድረግና የአየር ንብረት ለውጥ የፈጠረውን ተጽዕኖ ከመቋቋምና የግብርናው ዘርፍ ላይ ያለውን ተግዳሮት ከመሻገር አኳያ ሌላው እየተከናወነ ያለው ተግባር የተፋሰስ ልማት ወይም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ነው:: ይሄ መርሃ ግብር ከተጀመረ ቆየት ያለ ቢሆንም፤ በልዩ ትኩረት እና የግብርናው ዘርፍ እድገት አቅምነቱን በልኩ ተገንዝቦ መሥራት የተጀመረው ከ2010 ዓ.ም በኋላ ነው::

ይሄ መርሃ ግብር በአንድ በኩል ለአካባቢ ጥበቃ ሥራው አቅም የሚሆን የደን ጥበቃ ተግባርን ያካትታል፤ በሌላ በኩል አፈር እንዳይሸረሸር የሚያደርጉ አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ አለፍ ሲልም የውሃ ሀብት ልማት (ለምሳሌ፣ የዝናብ ውሃን በማቆር ምንጮችን የማጎልበት) ሚናን ይወጣል:: በዚህ መልኩ በርካታ የተራቆቱ አካባቢዎች አገግመዋል፤ ተራሮች ለምተዋል፤ የከርሰ ምድር ውሃ ጨምሯል፤ አያሌ ምንጮችም ጎልብተዋል::

እናም በየዓመቱ በበጋ ወቅት ላይ በሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ በሁሉም አካባቢዎች በሚከናወኑ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በሚሊዮን ሄክታር የሚገመት መሬት እንዲያገግም በማድረግ ለግብርናው ሥራ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል:: በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በሰብል ልማትና በእንስሳት መኖ ልማት ዘርፍ አያሌ ቱሩፋቶችን ለአርሶና አርብቶ አደሩ አስገኝቷል፤ እያስገኘም ነው::

ዘንድሮም ይሄው መርሃ ግብርን እንደ ሀገር በመተግበር ላይ ሲሆን፤ መርሃ ግብሩም የአፈር ሀብትን ጠብቆ መጠቀምን፣ የውሃ አቅም ማጎልበትን፣ አካባቢያዊና ሥነምህዳራዊ ሚዛንን መጠበቅን ማዕከል አድርጎ የሚከናወን ነው:: ይሄ ሲሆን ደግሞ እንደ ሀገር በግብርናው ዘርፍ እንዲገኝ በሚጠበቀው ውጤት ውስጥ ከፍ ያለ አበርክቶውን እውን ማድረግ ይቻላል።

በዚሁ መነሻነትም በቅርቡ “የአፈር ሀብታችን ለብልፅግናችን!” በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም ሀገር አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ሲምፖዚየም ተካሂዶ ነበር። በሲምፖዚየሙም፣ በደን መጨፍጨፍ ምክንያት የደረሱ ጉዳቶች፤ ችግሩን ከመቋቋም አኳያ ባለፉት ዓመታት በተፈጥሮ ሀብት ልማት የተሠሩ ተግባራትና የተገኙ ስኬቶች እንዲታወቁ ተደርጓል::

ለአብነትም፣ በደን መጨፍጨፍ ምክንያት የተራቆቱ አካባቢዎች ሀገሪቱን ለምግብ ዋስትና እጥረት እና ለአየር ንብረት ለውጥ ማጋለጡ በችግርነት የተነሳ ሲሆን፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍም ባለፉት ስድስት ዓመታት በዘለቀው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር 40 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል የተራቆቱ አካባቢዎች መልሰው እንዲያገግሙ ማድረግ መቻሉን በስኬት ተገልጿል። በዚህም ዓመትም 5 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሥነ-ሕይወታዊ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ እንደሚሸፈን ተመላክቷል::

የሲምፖዚየሙንም ሆነ የአካባቢ ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራውን አስመልክቶ የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየው፤ በዘርፉ እስከ አሁን በተከናወነው ሥራ 33 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት መልሶ እንዲያገግም ተደርጓል:: ከዚህ ውስጥ 21 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታሩ በማኅበረሰቡ ተሳትፎ የለማ ነው::

በሰምንኛው የሀገር አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ሲምፖዚየም ላይ የተገኙት እና “የአፈር ሀብታችንን ለብልፅግናችን ለማዋል እንረባረብ” የሚል መልዕክት ያስተላለፉት የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ እንዳመለከቱት፤ የተፋሰስ ልማቱን ማስፋት የአፈር ሀብቱን ለሀገራዊ ብልፅግና ማዋል እንደመሆኑ ለዚህ ሥራ ሁሉም ሊተባበር ይገባል::

**የተራራ ልማትና ሌሎች የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭነትን ለመከላከል፣ የውሃና ብዝኃ ሕይወት ሀብትን ለመጠበቅ ብሎም ለአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ የማይበገር ከባቢና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የጎላ ሚና ስላላቸው ይሄው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ነው መረጃው ያመላከተው**

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ገጻቸው ባጋሩት መረጃ መሠረትም፤ እንደ ሀገር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ግብን ለማሳካት በየዓመቱ ከ14 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን በማሳተፍ መጠነ ሰፊ የተፋሰስ ልማት ተግባራትን በማከናወን አመርታዊ ለውጥ መጥቷል። የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብትና የተፋሰስ ልማትን በመተግበርም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ የመገንባት ቁርጠኝነት ማሳየት ተችሏል::

በተሠራው ሥራም የተራቆቱ አካባቢዎች አገግመዋል፤ የአፈር መከላት ቀንሷል፤ የደን ሽፋኑም ወደ 23 ነጥብ ስድስት በመቶ አድጓል:: አርሶ አደሩ የተፋሰስ ልማት ውጤቶችን በመጠበቅና በባለቤትነት በመያዙ የንብ ማነብ፣ የእንስሳት ርባታ፣ የመስኖ ልማት እና የፍራፍሬ ልማትን በመተግበር ተጠቃሚ ሆኗል፤ በዘላቂነትም እየተጠቀመ ነው::

ይሄ ውጤት የተገኘውም በመንግሥት ቁርጠኛ አመራር፣ በዘርፉ ባለሙያዎች ያላሰለሰ ጥረት እና በኅብረተቡ የላቀ ተሳትፎ እንዲሁም በአጋር አካላት እገዛ ጭምር መሆኑን የጠቆሙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን፤ ይሄንኑ ስኬት ከማስቀጠል አኳያ በዚህ ዓመትም በአራት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ላይ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራ እንደሚካሄድ፤ ለዚህም ሁሉም አካል የተለመደ ሚናውን እንዲወጣ መልዕክት አስተላልፈው ነበር::

ይሄን መነሻ በማድረግም የግብርና ሚኒስቴር ዘርፉን እንደሚመራ ተቋም ከፊት ቀድሞ፤ ክልሎችም ይሄንኑ አደራ ተቀብለው በመከተል የየድርሻቸውን ለመወጣት እየሠሩ ይገኛል:: በዚህ ረገድ በሁሉም ክልሎች በአጠቃላይም በመላው ሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በሰፊ ንቅናቄ እና ከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ ታግዘው በመከናወን ላይ ይገኛሉ::

ይሄንን መርሃ ግብር ቀድመው ከጀመሩ ክልሎች መካከል አንዱ የሆነው የኦሮሚያ ክልል ሲሆን፤ ክልሉ በዘንደሮው መርሃ ግብር ሦስት ነጥብ ሦስር ሚሊዮን ሄክታር ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ለማካሄድ አቅዶ እየሠራ መሆኑን ቢሮው አስታውቋል::

የቢሮው መረጃ እንደሚያመለክተው የተፈጥሮ ሚዛንን ለማስጠበቅ እና የአፈር ለምነትን ለማሳደግ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ያለውን ከፍ ያለ ሚና በመገንዘብ እና ለሥራው አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ከዘጠኝ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የክልሉ ነዋሪዎች የሚሳተፉበት ሥራ ይከናወናል። ለዚህም ለግብርና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፤ ለሥራው የሚውሉ የቁፋሮና ሌሎች መሳሪያዎችም ተዘጋጅተዋል::

ከዚህ ባሻገርም፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራ የሚከናወንባቸው ተፋሰሶች የተለዩ ሲሆን፤ በመርሃ ግብሩ በሚኖር የነቃ የሕዝብ ተሳትፎና አበርክቶ ዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የሚገመት ሥራ እንደሚሠራ ይጠበቃል::

በተመሳሳይ፣ በቤኒሻንጉል ጉመዝ ክልል በ53 ሺህ ሄክታር ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ሥራ የተጀመረ ሲሆን፤ ለሥራው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችም ተዘጋጅተዋል:: የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራ የሚከናወንባቸው 429 በላይ ተፋሰሶችም ተለይተዋል:: በመርሃ ግብሩም 247 ሺህ ዜጎች እንደሚሳተፉ ይጠበቃል::

በሐረሪ ክልልም በዘንድሮ ዓመት በ16 ተፋሰሶች 900 ሄክታር መሬት ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። ለዚህ ደግሞ አርሶ አደሩ የተፋሰስ ልማት ሥራ ጠቀሜታውን በመረዳቱ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራን ከዓመት ዓመት እያስፋፋ ይገኛል::

ቀደም ሲል በክልሉ በርቀት ተቆፍሮ ይገኝ የነበረው የከርሰ ምድር ውሃ በቅርበት እንዲገኝ ማስቻሉ፤ በዚህም አርሶ አደሩ የመስኖ ልማት ሥራውን በማጎልበት የምግብ ዋስትናውን እንዲያረጋግጥ አስተዋጽኦ ማድረጉ፣ ለተገኘው ውጤት በማሳያነት የሚጠቀሱ ናቸው:: በዚህ መነሻነት በዘንድሮው የተፋሰስ ልማት ሥራም የተለያዩ የአፈርና ውሃ እቀባ ሥራዎች ይከናወናሉ:: ለዚህም አስፈላጊው የዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል::

በተመሳሳይ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ከ421 ሺህ 378 ሔክታር መሬት ላይ የተፋሰስና ልማት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች እንደሚከናወን የክልሉ ግብርና ቢሮ መረጃ ያሳያል::

የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት መርሃ-ግብሩ በክልሉ በተለዩ አንድ ሺህ 391 የማኅበረሰብ ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የሚከናወን ሲሆን፤ በእነዚህም ከሰውና እንስሳት ንክኪ ነፃ አድርጎ የማልማት ሥራ ይከናወናል:: በመርሃ ግብሩም ከሁለት ነጥብ 39 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በነፃ የጉልበት አስተዋፅዖ እንደሚሳተፍም ይጠበቃል::

በክልሉ ከመደበኛ የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ እንዲሁም የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራ በተጨማሪ፤ ለተራራ ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት “በአንድ ዞን አንድ ተራራ መልሶ የማልማት” ክልላዊ ኢኒሼቲቭ በማስተዋወቅ ወደ ሥራ ተገብቷል::

በዚህም በክልሉ አራት ሺህ 350 ሔክታር የተራቆቱ ተራሮች ሥነ-ምኅዳር በደንና የፍራፍሬ ችግኞች መልሶ የማልማት ተግባር ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተሠራ ሲሆን፤

የተራራ ልማትና ሌሎች የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭነትን ለመከላከል፣ የውሃና ብዝኃ ሕይወት ሀብትን ለመጠበቅ ብሎም ለአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ የማይበገር ከባቢና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የጎላ ሚና ስላላቸው ይሄው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ነው መረጃው ያመላከተው::

መርሃ ግብሩ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልልም፣ ለአንድ ወር የሚዘልቅ እና “የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ለኅብረተሰብ ብልፅግና” በሚል መሪ ሃሳብ የሚካሄድ ሲሆን፤ በክልሉ የዘንድሮው የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራ በአንድ ሺህ 301 ንዑስ ተፋሰሶች፣ በ280 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሚካሄድ ይሆናል። ከአንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ይሳተፉበታል::

በእነዚህ እና ሌሎችም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በዚህ መልኩ በልዩ ትኩረት እና በሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ በንቃት የሚከናወነው የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራ ታዲያ፤ እንደ ሀገር የሚኖረው ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ተኪ የሌለው ነው:: በተለይም የግብርናው ዘርፍ ላይ እንዲሆን የሚጠበቀው እምርታዊ ለውጥና ውጤት እንዲሳካ በማድረግ በኩል ድርሻው ከፍ ያለ ነው::

ለአብነት፣ የተፋሰስ ልማት ሥራውን ተከትሎ የንብ ማነብ ሥራ ይከናወናል:: ለእንስሳት እርባታም ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል:: ከመስኖ ልማት ሥራ አመቺ የሆነ የውሃ ማጎልበት አቅም ፈጥሯል። ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማትም ምቹ ነው:: ይሄ ማለት ደግሞ የሌማት ቱሩፋት ኢኒሼቲቭ አንዱ አካል ሆነ ማለት ነው::

ከዚህ አኳያ መርሃ ግብሩ ቀጣይም፣ ውጤታማነቱ የተረጋገጠም ሆኖ እንዲቀጥል ዘርፈ ብዙ ክትትልና ድጋፍ ያስፈልገዋል:: በዚህ ረገድ፣ በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀው የአረንጓዴ ዐሻራና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር አዋጅን ጉልህ አበርክቶ ይኖረዋል። በመሆኑም በአንድ በኩል የኅብረተሰቡን አቅም በመጠቀም፤ በሌላ በኩል በሕግና አሠራር በመደገፍ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራውን የግብርናው እድገት አቅምነት ማጎልበት በእጅጉ የተገባ ነው::

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አበረታች የኢንቨስትመንት ጉዞ

**አንተነህ ቸሬ**

ቀደም ሲል በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር የነበሩትን የምዕራብ ኦሞ፣ የቤንች ሸኮ፣ የከፋ፣ የዳውሮና የሸካ ዞኖች እና የኮንታ ልዩ ወረዳን (ልዩ ወረዳው አሁን በዞን ደረጃ ተደራጅቷል) በአንድነት በመያዝ በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ 11ኛው ክልላዊ መንግሥት ሆኖ የተዋቀረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል፤ በተፈጥሮ ሀብት የታደለ አካባቢ ነው፡፡

ክልሉ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጣና ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎችም የሚበቃ የተትረፈረፈ ሀብት አለው፡፡ ዓመታዊ ሰብል፣ ቡናና ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ሌሎች የወጪ ንግድ ምርቶች (Export Items)፣ ኢንዱስትሪ እና አገልግሎት ዘርፎች በክልሉ በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያስችሉ የምጣኔ ሀብት መስኮች ናቸው፡፡ በተለይም የቡና፣ የሻይ ቅጠል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የማዕድናት ሀብትና ለም መሬት ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያነሳሳ እና የሕዝብን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር መልካም አጋጣሚና ፀጋ ነው፡፡

ክልሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚን በብርቱ የሚደግፉ ምርቶች መገኛ ነው። ከፍተኛ የቡናና የማዕድን ሀብቶችን የያዘው ይህ ክልል፤ ሀብቱ ከክልሉ አልፎ ለሀገርም የሚተርፍ ትልቅ ፀጋ ነው፡፡ ክልሉ አስደናቂ የሆነ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ልምላሜና የተፈጥሮ ሀብት ያለው በመሆኑ የባለሀብቶችን ትኩረት የሚስብ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

የክልሉን ሀብቶች ለመለየት የሚደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ክልሉ ለዓመታዊ ሰብሎች፣ ለቡናና ቅመማ ቅመም እና ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚውል ሰፊና ምቹ መሬት አለው፡፡ በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎችም የኢንቨስትመንት መዳረሻና አማራጭ መሆን የሚችል አካባቢ ነው፡፡

ክልሉ ወርቅን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድናት ባለፀጋ እንደሆነም የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከወርቅ ማዕድን በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል በክልሉ በዳውሮ እና በኮንታ አካባቢዎች በስፋት ይገኛል። ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የብረትና የድንጋይ ከሰል ማዕድናትም ሌላው በክልሉ የሚገኙ ሀብቶች ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ማዕድን ለማዕከላዊ ገበያ ከሚያቀርቡ የሀገሪቱ አካባቢዎች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡ በክልሉ ገና በጥናት ያልተለዩ ብዙ ሀብቶች አሉ፡፡ ኦፓልና ሌሎች ማዕድናትም በክልሉ ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል፡፡

በርካታ ባለሀብቶች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተዋል፡፡ ክልሉ ከተዋቀረ አጭር እድሜ ቢኖረውም ኢንቨስትመንቱ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሰፊ ጥናትና ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው በኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ለማበረታታት የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና የካቢኔ አባላትን ጭምር ያሳተፈ የንቅናቄና የፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ተሠርቷል፡፡ ክልሉ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ የተሠሩት የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራዎች በክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በ2016 የበጀት ዓመት አበረታች የኢንቨስትመንት አፈፃፀም ማስመዝገቡንና በ2017 የበጀት ዓመትም ይህን አፈፃፀሙን ለማሳደግ እየሠራ እንደሚገኝ የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ክልሉ በኢንቨስትመንት ዘርፍ በ2016 የበጀት ዓመት ያስመዘገባቸውን ስኬቶች በ2017 የበጀት ዓመትም አጠናክሮ ለማስቀጠል እቅድ አዘጋጅቶ በትግበራ ላይ እንደሚገኝና በ2017 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ጥሩ አፈፃፀም እንዳስመዘገበ የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ኃላፊና የኢንቨስትመንት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከበደ ተስፋዬ ያስረዳሉ፡፡




እሳቸው እንደሚገልጹት፣ በክልሉ ለኢንቨስተሮች ፈቃድ በመስጠት እንዲሁም ባለሀብቶችን ወደ ሥራ በማስገባት የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳለጥ፣ ባለፉት ስድስት ወራት፣ በግብርና፣ በማምረቻ እና በአገልግሎት ዘርፎች አራት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 77 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 54 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

የኢንቨስትመንት መሬት አቅምን በመለየት ረገድ፣ ስምንት ሺ ሄክታር መሬት ለማጥናት ታቅዶ፣ ከሰባት ሺ 635 ሄክታር በላይ መሬት ማጥናት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዘጠኝ ሺ 644 ሄክታር መሬት ለባለሀብቶች ለማስተላለፍ እቅድ ተይዞ ነበር፤ ከ10ሺ 400 ሄክታር በላይ መሬት እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ በስድስት ወራት ውስጥ ለ37ሺ993 ዜጎች (1561 ቋሚ እና 36432 ጊዜያዊ) የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፣ 37ሺ788 ዜጎችን (678 ቋሚ እና 37ሺ110 ጊዜያዊ) የሥራ እድል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን በቴክኖሎጂ በታገዘ አሠራር የባለሀብቶችን መረጃ የማጥራት ሥራ ተሠርቷል፡፡ በዚህም የባለሀብቶች ቁጥር፣ የማልማት አቅም፣ የስምሪት ዘርፎችና ሌሎች መረጃዎች ተጣርተው እንዲደራጁ እና ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው ላሉ የአስተዳደር አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ከባለሀብቶች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት የአገልግሎት አሰጣጡንና የመሠረተ ልማት አቅርቦቱን ቀልጣፋና የተሻለ በማድረግ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለመጨመርና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ውጤታማነት ለማሻሻል እየተሠራ መሆኑን አቶ ከበደ ይገልፃሉ፡፡ እንደሳቸው ማብራሪያ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በየደረጃው የሚገኙ የክልሉ ተቋማት ለባለሀብቶች መረጃ ከመስጠት ጀምሮ የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ለማስፈን ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች በጥልቀት እንዲታዩ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፈቃድና መሬት በፍጥነት እንዲሰጡ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በክልል ደረጃ የኢንቨስትመንት ዘርፍ አጠቃላይ አሠራርን በኦንላይን (Online) ላይ የተመሠረተ ለማድረግ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። የማበረታቻ አሠራር በኦንላይን የታገዘ ነው፡፡ የኦንላይን አሠራርን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የበጀት እጥረት ትልቅ ፈተና ሆኗል፡፡

> **ባለፉት ስድስት ወራት ባለሀብቶችን በማስተባበር 52 ኪሎ ሜትር ተደራሽ መንገድ ለመሥራት ታቅዶ፣ 55 ኪሎ ሜትር መንገድ መሥራት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ 900 የኅብረተሰብ ክፍሎች በቡና ልማት ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ ሆነዋል**

አቶ ከበደ እንደሚያስረዱት፣ ቀደም ሲል መሬት ወስደው ያላለሙ ባለሀብቶችን በተመለከተ፣ የመሬት ኦዲቲንግ ተግባር በከፍተኛ ትኩረት እየተሠራ ነው። ቀደም ሲል ጀምሮ መሬት ወስደው በማያለሙ እንዲሁም ለማኅበረሰቡ አገልግሎት በማይሰጡ ባለሀብቶች ላይ ሕጋዊ ርምጃ መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ የመሬት ኦዲት ይደረጋል፡፡

‹‹እንዲህ ዓይነት ርምጃዎች ካልተወሰዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በታለመላቸው የጊዜ ገደብ ላይጠናቀቁ ይችላሉ፡፡ ይህ የኦዲቲንግ ሥራ መሬት ተረክበው የማያለሙ ባለሀብቶች በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ ወይም መሬቱን ለሌሎች አልሚዎች ለማስተላለፍ ያግዛል። የኢንቨስትመንት አዋጁ ለባለሀብቶች የተሰጡ መሬቶች ሊነጠቁ የሚችሉባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የባለሀብቶች የሥራ እንቅስቃሴዎች በእነዚህ መስፈርቶች መሠረት ተገምግመው ቅድመ ሁኔታዎቹ ካልተሟሉ መሬት እንዲነጠቁ ይደረጋል›› ይላሉ፡፡

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ካሏቸው ፋይዳዎች መካከል አንዱ ፕሮጀክቶቹ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረጋቸው ነው፡፡ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግሥት ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ ሲያስገባ ባለሀብቶች በተለያዩ መንገዶች የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ በማሰብ ነው፡፡ማኅበረሰቡ ከኢንቨስትመንት ሥራዎች በሥራ እድል ፈጠራ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በገበያ እድል ተጠቃሚ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

በዚህ ረገድ በክልሉ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለክልሉ ህብረተሰብ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች እንዳሏቸው አቶ ከበደ ይገልፃሉ፡፡ ‹‹በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ‹አንድ ባለሀብት ወደ አንድ አካባቢ ሲመጣ ለማኅበረሰብ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድን ነው?› የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሻ ዐቢይ ጉዳይ ነው›› የሚሉት አቶ ከበደ፣ ይኸው ጉዳይ የክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግባር አካል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

‹‹ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት መስክ ሲሰማሩ የሥራ እድል መፍጠር አለባቸው፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በቴክኖሎጂ ሽግግር አስተዋጽኦ የማያበረክቱ ከሆነ፣ የኅብረተሰቡ ኑሮ ሊለወጥና ሊሻሻል አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ የኢንቨስትመንት ተግባራት ዘላቂ ፋይዳ እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ባለሀብቶች ለቴክኖሎጂ ሽግግር ትኩረት እንዲሰጡ ጥረት ይደረጋል›› ይላሉ፡፡

እሳቸው እንደሚያብራሩት፣ በክልሉ የሚገኙ ባለሃብቶች በሚያከናውኗቸው የኢንቨስትመንት ተግባራት አማካኝነት የሥራ እድል ከመፍጠር በተጨማሪ፣ ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ። ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ሥራዎቻቸውን በሚሠሩባቸው አካባቢዎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ተግባራትን ስለሚያከናውኑ የአካባቢው ኅብረተሰብ በዚህ ተግባር በኩል ተጠቃሚ ይሆናል። ይህ የማኅበረሰቡ ተጠቃሚነት ማኅበረሰቡ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረው አድርጓል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት ባለሀብቶችን በማስተባበር 52 ኪሎ ሜትር ተደራሽ መንገድ ለመሥራት ታቅዶ፣ 55 ኪሎ ሜትር መንገድ መሥራት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ 900 የኅብረተሰብ ክፍሎች በቡና ልማት ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ ሆነዋል።

በኢንቨስትመንት ሥራ አመራር ረገድ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ለሌሎች ክልሎች አርዓያ ሊሆን የሚችልባቸው መልካም ተሞክሮዎች እንዳሉት አቶ ከበደ ይገልፃሉ፡፡ ‹‹የፕሮጀክት ግምገማ ሥርዓታችን አጭር ነው፡፡ ወደ ክልሉ የሚመጡ የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ ያገኛሉ። ቅሬታዎችንም በፍጥነት የመፍታት አሠራር አለን። እነዚህ አፈፃፀሞች ለሌሎች ክልሎችም ተሞክሮ ይሆናሉ ብለን እንምናለን›› ይላሉ፡፡

እምቅ የኢንቨስትመንት አቅም ያለው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልሉ፣ ባለሀብቶችን ለመሳብ በሚያደርገው ጥረት ላይ መሰናክል የፈጠሩበት ችግሮች እንዳሉ አቶ ከበደ ያስረዳሉ። ‹‹በፌዴራል ደረጃ የሚወጡ አንዳንድ ሕጎች ለኢንቨስትመንት መሰናክል ሲሆኑ ይስተዋላሉ። ለምሳሌ ብድር የሚመቻቸው በመስኖ ለሚያለሙ ባለሀብቶች ነው መባሉ በክልሉ ኢንቨስትመንት ላይ አሉታዊ ጫና ያሳድራል፡፡ በክልሉ ዓመቱን ሙሉ ዝናብ የሚዘንብበት እና መልከዓ ምድሩም ለመስኖ አመቺ አይደለም፡፡ ስለዚህ ክልላዊ ነባራዊ ሁኔታውን ታሳቢ ያደረጉ የሕግ ማሕቀፎች መዘጋጀት አለባቸው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፣ የመሠረተ ልማት (መንገድ፣ መብራት እና የመሳሰሉ) እጥረት እና ባለሀብቶች በክልሉ ውስጥ አምርተውና እሴት ጨምረው የአካባቢውን ስም በምርቶች ብራንድ (Brand) ለማስጠራት የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ መሆኑ በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ ጫና እያሳደሩ የሚገኙ ተግዳሮቶች መሆናቸውን አቶ ከበደ ይገልፃሉ፡፡

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## «እኛ ለእኛ »

ሀብታሙ ባንታየሁ

"በእኛ ጊዜ ዳቦ ፈላጊዎች ማህበር ( ዳ . ፈ. ማ ) የሚባል ማህበር ነበረን" አሉ የትናንቱን የእርስ በርስ መደጋገፋቸውን ዛሬ ላይ ሆነው በምልሰት እያስታወሱ። "ለህይወት የሚበጅ ቁም ነገር ለትዝታ የሚተርፍ ማህደር የሰነቅነውና ለዘመን አሻራችን እርሾ የጣልነው ሮጠን ባልደከምንበት ብርቱ የሥራ ሞራል በታጠቅንበት በወጣትነት ዕድሜያችን ነበር፡፡

ዛሬ ለዳቦ ፈላጊዎች ማህበር የጣልነው እርሾ አልፎ ተርፎ ብዙ ዓይነ ሥውራን እጃቸው ከአፋቸው ሳይገናኝ እንዳያድር (ዳቦ ቆርሶ ለማደር) ምክንያት ሆነናል። ዓይነ ሥውራን ተምረው፣ተመርቀው ለሥራ ቅጥር እስኪበቁ ድረስ ከጥገኝነት በመላቀቅ መልሰውም እጃቸውን ለልመና እንዳይዘረጉ ድጋፍ የምናደርግበት ሆኗል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን በቀለም ትምህርቱም ያልተሳካላቸው ዓይነ ሥውራን ያላቸውን የዕደ ጥበብ ችሎታ በሥልጠና እንዲያዳብሩ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ግብረ ሠናይ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የሥራ እድል እንፈጥርላቸዋለን" ይላሉ፤ ዛሬን በሀገረ አሜሪካ ቨርጂንያ ግዛት ኑሯቸውን ያደረጉት ዶክተር ካሳሁን ይበልጣል።

ዶክተር ካሳሁን ከ15 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ዓይነ ሥውራን ብሔራዊ ማህበርን በፕሬዚዳንትነት መርተዋል፤ ዓይነስውራን የተሻለ ነገን እንዲያዩ ደክመዋል። ከሌሎች የማህበሩ አመራሮች ጋር ሆነው ማህበሩን ጠንካራ ለማድረግ የአቅማቸውን ሁሉ ጥረት አድርገዋል። አሁን ስልጣኔ በገባው የተሻለ ሀገር በመኖራቸው ግን አይነስውራን ወገኖቻቸውን ከመጎብኘት አራቁም፡፡ እግራቸው የኢትዮጵያን ምድር ባይረግጥ ልባቸው ግን እዚሁ ነው። ለማህበሩ ይበጃል ያሉትን ዓይነስውራኑን ይደግፋል ያሉትን ሃሳብ ሁሉ በማካፈል ጭምር ከአብሮነት አራቁም።

"ለህይወት የሚበጅ ቁም ነገር፣ ለትዝታ የሚተርፍ ማህደር የሰነቅነውና ለዘመን አሻራችን እርሾ የጣልነው ሮጠን ባልደከምንበት፣ ብርቱ የሥራ ሞራል በታጠቅንበት በወጣትነት ዕድሜያችን ነበር

ዶክተር ካሳሁን ጥር 09 ቀን 2017 ዓ.ም ማህበሩ "እኛ ለእኛ" ሲል ባዘጋጀው የበጎ አድራጎት መርሀ ግብር ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው ነበር፡፡ በቦታው መገኘት ብቻም ሳይሆን እርሳቸው በነበሩበት ወቅት የነበረውን እርስ በርስ መረዳዳት ምን ይመስል እንደነበርም ሃሳባቸውን አጋርተዋል ፤ "ገንዘብና ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን ጊዜና እውቀትን መስጠትም በጎ አድራጊነት ነው። በእኛ ዘመን እንደየዕድሜ ቅደም ተከተላችን የደረስንበትን የቴክኖሎጂ አድማስ አንዱ ለሌላው የእውቀት ሽግግር በማድረግ አይነ ሥውራን በሥራው አለም የተሻለ ተወዳዳሪ እንድንሆን አስችሎናል" ብለዋል ፡፡

ዶክተር ካሳሁን ለአሁኖቹ የመድረኩ ተሳታፊዎችም ‹‹እናንተም ዛሬ የጀመራችሁት ‹እኛ ለእኛ› የተሰኘውና ለመተሳሰብ የበቃችሁበት ዝግጅት ዓላማና ግቡ ተስማምቶ ሞራላችሁን አበርትቶ፤ ነጋችሁን ብሩህ እንዲያደርግ ጠንካራ ትግል ይጠበቅባችኋል" ሲሉ ምክርና መልዕክታቸውን ያደርሳሉ፡፡

በእሳቸው እግር ተተክተው ፈለጋቸውን ያስቀጠሉት የኢትዮጵያ ዓይነሥውራን ብሔራዊ ማህበር የወቅቱ ፕሬዚዳንት አቶ ፋንታሁን መንግሥቴም በፕሮግራሙ መክፈቻ ላይ ንግግር አሰምተዋል፤ "ምንም እንኳን ይህ መድረክ የመጀመሪያችን ቢሆንም አንዳችን ለአንዳችን ‹አለሁ› መባባላችን ‹ድር ቢያብር አንበሳ ያስር› ያልነውን ተረት በተግባር እንድንኖረው ነው። መንግሥት ያመቻቸልንን እድል ለመጠቀም እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ ከስኬት ከፍታ ላይ ለመቀመጥ ዛሬ ያካሄድነው ዝግጅት ማህበራዊ መስተጋብራችንን የሚያሳካ ይሆናል። ከዚህም ባለፈ ይህ አጋጣሚ የልቦና ብቁነታችንን ፣ የሞራል ተነሳሽነታችንን ያሳድግልናል" ብለዋል፡፡

የማህበሩ ዋና ተግባር የሕገ ደንቦች፣ አዋጅና መመሪያዎች፣ የፖሊሲ ለውጦች ሲኖሩ ክትትል በማድረግ ዓይነሥውራንን አካታች የኢኮኖሚ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሥርዓትን መገንባት መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡

ይህ ሂደት በዘላቂነት የሚሠራ ቢሆንም እንዲህ አይነቱ መሰል ዝግጅት የዓይነስውራኑን ህብረት ለማፅናትና ግንኙነቱን ለማጠንከር ስለሚረዳ ቀጣይነት እንዲኖረው የድርሻችንን ኃላፊነት እንወጣለን ይላሉ ፡፡

የማህበሩ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዚዳንት የነበሩት ቃል ኪዳን ሺመልስም "እኛ ለእኛ" የበጎ አድራጎት ዝግጅትን መነሻና መዳረሻ ተከትሎ መነሻ ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ከድህነት ወለል በታች ያሉ ዓይነ ሥውራንን በልተው እንዲያድሩ ማስቻል፣ በማህበሩ በኩል የሥራ እድል ፈጠራን ማስፋት፣ ከሌሎች በጎ አድራጎት ሰጪ አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ የሚሉ ነጥቦችን በዳሰሳቸው አንስተዋል፡፡

ከዚህ መርሀ ግብር በኋላ ሃሳቡን ከመጠንሰስ አንስቶ እስከ ፍፃሜው ድረስ ድጋፉን ለማሰባሰብ በቀዳሚት የተሰለፉት የዓይነ ሥውራን መምህራን የሴቶች ዘርፍ ተጠሪ የሆኑት አለሚቱ ተፈራ ድጋፉን በማሰባሰብ ሂደት የተገኘውን ውጤትና ያጋጠሙ ችግሮችን በሪፖርታቸው አመላክተዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ሥራው የመጀመሪያ እንደመሆኑ የተገኘው ውጤት ከተገመተው በላይ ይሁን እንጂ የበለጠ አመርቂ ሥራ ለማከናወን ከሁሉም ዓይነ ሥውራን ድጋፉን ለማሰባሰብ የቦታ ርቀትና የሰው ኃይል ማነስ ክፍተቶች መስተዋላቸውን ጠቁመዋል፡፡ የጊዜ እጥረትም ዋነኛ ችግር መሆኑንም አውስተዋል፡፡

የመምህራን ዘርፍ ተጠሪው መምህር ዋለ ደሴ እንደሚሉትም ለ25 ሴቶችና ለ15 ወንዶች በድምሩ ለ40 አዋቂ ዓይነ ሥውራን እንዲሁም ለሰባት ሴቶች እና ለአምስት ወንዶች በድምሩ ለ12 ዓይነ ሥውራን ልጆች በጠቅላላው ለ52 ሰዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

"ሀገርና ትውልድ ግንባታ ላይ ጉልህ ሚና እንዲኖረው መምህር ዋለ የመድረኩን አስፈላጊነት ተዓማኒ መሆኑን ሳይገልጹ አላለፉም፡፡ የዕለቱን ዝግጅት መድረኩንና ማህበሩን ያቋቋመው ወጋገን ባንድ የኪነ ጥበብ ሥራዎች አድምቀታል፡፡

በመጨረሻም የበጎ አድራጎት ሥራው የተሳካ ይሆን ዘንድ "እኛ ለእኛ" ብለው ለለገሱ ለማህበሩ አባላት የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል፡፡ ፌቨን አሸብርና ገበየሁ ደረጀም የተደረገላቸው የገንዘብና የአልባሳት፣ የፅዳት መጠበቂያና የትምህርት ቁሳቁሶች የእለት ችግራቸውን ለመቅረፍ እንደሚያግዛቸው አስበው ምሥጋና ቸረዋል፡፡ እነዚህ ወንድም እህቶቻቸው "ሰው ያለሰው፤ እህል ያለመንጋጋ አይደቅ" የሚለውን ብሂል በተግባር እንዳስመሰከሩም በኩራት ይገልጻሉ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ለካፒቶል ዓመጽ ሁከት ቀስቃሾች የተደረገው ይቅርታ

ትራምፕ በመጀመሪያ ቀን የሥልጣን ዘመናቸው ለካፒቶል ዓመጽ ሁከት ቀስቃሾች ይቅርታ ማድረጋቸው ተገልጿል፡፡ በዚህም ሁሉንም ሁከት ፈጣሪዎች ነፃ ያወጣ እና በአሜሪካ ታሪክ ትልቁን የወንጀል የምርመራ ሥራ የሰረዘ ይቅርታ አስተላልፈዋል ተብሏል።

ትራምፕ ጥር 12 ቀን 2017 ዓ.ም የሰጡት ፕሬዚዳንታዊ ትዕዛዝ አንዳንድ እስረኞች ከጠየቁት የመንግሥት የገንዘብ ካሳ ክፍያ ውጪ ሁከት ፈጣሪዎቹን እና ደጋፊዎቻቸውን ሲጠይቁ የነበሩትን ነገሮች በሙሉ የሰጠ ነው ማለት ይቻላል ሲሉ አስተያየት ሰጪዎቹ ተናግረዋል።ትራምፕ ጥር 13 ቀን 2017 ዓ.ም በዋይት ሃውስ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ "እነዚህ ሰዎች በእስር ቤት ዓመታትን በመጥፎ ሁኔታ አሳልፈዋል።" አስጸያፊ እስር ቤት ነው። በጣም አሰቃቂ ነበር። ኢሰብአዊ ነው ብለዋል።



በርከት ያሉ በሁከቱ የተያዙ ሰዎች በታሰሩበት በዋሽንግተን ዲሲ እስር ቤት፤ በተከሳሾቹ እና በደጋፊዎቻቸው በሚዘወሩ የማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ብዙዎች ደስታቸውን ገልጸዋል።ማክሰኞ የተለቀቀው የፕራውድ ቦይስ መሪው ኤንሪኬ ታሪዮ እናት ስለልጇ በመደበኛነት መረጃዎችን ስታጋራ ቆይታለች።

"የእኛ ፕሬዚዳንት ልጄን እና ለሌሎቹም ሕይወታቸውን መልሰዋል! እንደገና መኖር ይችላሉ! እንደገና ንጹህ አየር ይተነፍሳሉ! እንደገና የፀሐይ ብርሃን ያገኛሉ" ስትል ዞኒ ታሪዮ 22 ዓመት ተፈርዶበት በፕሬዚዳንቱ ይቅርታ በነጻ ስለተለቀቀው ልጇ ጽፋለች።

ከዋሽንግተን ዲሲ እስር ቤት ከተፈቱት አንዷ የፔንስልቬንያ ነዋሪ የሆነችው ራቸል ፓውል ስትሆን፤ የካፒቶል ሂል መስኮትን በበረዶ መጥረቢያ በመስበር ከአራት ዓመት በላይ እስራት ተፈርዶባት ነበር። እንደገለጸችው ከሆነ አሁን ለልጇ ልደት በሰዓቱ ቤት እንደምትደርስ ተናግራ፤ ትራምፕ የገቡትን ቃል በመጠበቃቸው "ከማስበው በላይ ለእኔ ትልቅ በረከት ናቸው" ስትል አመስግናቸዋለች።

አንዳንድ ታዛቢዎች፣ የፖሊሲ ባለሙያዎች እና የሁከት ፈጣሪዎቹ ጠበቆች ጭምር በፕሬዚዳንቱ የትዕዛዝ መጠን ተገርመዋል።ይቅርታውን የሚቃወመው እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፐብሊክ ሲቲዝንን በፕሬዚዳንት የሚመሩት ሊዛ ጊልበርት "አመጽ በፈጸሙት እና ባላጠፉት መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት እንድንችል አጠቃላይ መግባባት ነበር" ብለዋል።

"ዶናልድ ትራምፕ በሕግ እና በሥርዓት ለሥልጣን ተወዳድረዋል። ስለዚህ ወንጀለኞችን ይቅርታ ለማድረግ እርምጃ ሲወስድ ማየት አስደንጋጭ እና አሳዛኝም ነው" ሲሉ ገልጸዋል። በጣም ከባድ በሆኑ ወንጀሎች የተከሰሱ 14 ሰዎች ቅጣታቸው ተቀይሮ ከእስር ቢለቀቁም ጥፋታቸው ተመዝግቦ ይቆያል ተብሏል።

የፍትህ ቢሮ ባወጣው ዘገባ አንድ ሺህ 583 ሰዎች ከአመጹ ጋር በተያያዙ ወንጀሎች ታስረዋል ተፈርዶባቸዋል።ከ600 በላይ የሚሆኑት ፖሊስን በማጥቃት፣ በመቃወም ወይም በማደናቀፍ የተከሰሱ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል 175 የሚሆኑት መሳሪያ በመጠቀም ወይም ፖሊስ ላይ ከባድ ጉዳት በማድረስ የተከሰሱ ናቸው ተብሏል።

አብዛኛዎቹ ጥፋተኛ ተብለው የተፈረደባቸው ሰዎች ፍርዳቸውን አጠናቀዋል ወይም ምንም ዓይነት እስር አልተላለፈባቸውም። እስካሁን በእስር ላይ የሚገኙት 250 የሚጠጉ ሰዎች ደግሞ መፈታት ጀምረዋል። ተጨማሪ ምርመራዎች ለማድረግ ኤፍቢአይ ቢያንስ 13 ተጠርጣሪዎችን እየፈለገ የነበር ቢሆንም ሂደቱ ይቋረጣል።

የሁከት ፈጣሪዎች ደጋፊዎች ይቅርታውን በተመለከተ ደስታቸውን ገልጸዋል። አመጸኞቹን "የጄ6 ታጋቾች" እና "የፖለቲካ እስረኞች" ከማለት ባለፈ ፖለቲካዊ ዓላማ ያለው እና ጭካኔ የሞላበት መሆኑን ጠቅሰዋል።

አንዳንድ እስረኞችን የወከለው ጠበቃው ኖርም ፓትስ እንደተናገረው ከሆነ "ይህ ክስተት ሀገሪቱን ያስፈራራል የሚለው አስተሳሰብ ከልክ ያለፈ ነው" ከማለት ባለፈ የኮንፌደሬት አማፂያን ከእርስ በርስ ጦርነት በኋላ ይቅርታ እንደተደረገላቸው ተናግሯል።

ለወንጀለኞች በሙሉ ይቅርታ መደረጉ ተቀባይነት እንደሌለው የሕዝብ አስተያየት መስጫዎች ይጠቁማሉ። በቅርቡ የተደረገ የአሶሼትድ ፕሬስ ጥናት እንደሚያመለክተው፤ ከ10 አሜሪካውያን መካከል ሁለቱ ብቻ ለአብዛኛዎቹ ይቅርታ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል።

በእለቱ በቡጢ የተመታ እና በርበሬ የተረጨበት የካፒቶል ፖሊስ አባል ዊንስተን ፒንግዮን እንዳለው ከሆነ፤ ይቅርታው "ያልተጠበቀ እና የሚያናድድ ነው" ብሏል።"በሀገሪቱም ሆነ በመላው ዓለም የፈጸሙት ነገር የታየባቸው እነዚህ በዳኞች የተፈረደባቸው ወንጀሎች በነፃነት እንደሚወጡ ማድረጉ ከዚህ በፊት ታይቶ የማያውቅ ነገር ነው" ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የስፖርት ፌስቲቫል ከነገ በስቲያ ይጀመራል

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የስፖርት ፌስቲቫል ከነገ በስቲያ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መካሄድ ይጀምራል። ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ተቋርጦ የነበረው ይህ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የስፖርት ፌስቲቫል ለአስር ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ በአምስት የስፖርት አይነቶች ፉክክሮችን እንደሚያስተናግድ ታውቋል።

የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበርና የውድድሩ አዘጋጅ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከትናንት በስቲያ በሰጡት የጋራ መግለጫ እንዳሳወቁት፣ ውድድሩን ከዓመታት በኋላ ለማስጀመር አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል።

ውድድሩን ዳግም ለማስጀመር ያህል በዘንድሮው ፌስቲቫል እግር ኳስ፣ አትሌቲክስ፣ ቼስ፣ ወርልድ ቴኳንዶና የባህል ስፖርቶች ብቻ ፉክክር እንደሚደረግባቸው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ አባይ በላይነህ ገልጸዋል። ከአርባ ዘጠኙ ተሳታፊ ዩኒቨርሲቲዎች አርባ ስድስቱ በእግር ኳስ እንደሚሳተፉ ማረጋገጣቸውንም ጠቁመዋል። የዩኒቨርሲቲዎች የስፖርት ፌስቲቫል ከዚህ በኋላም በቀጣይነት እንዲካሄድ የስፖርት ማህበሩ ቁርጠኛ መሆኑን ጠቁመው፤ ፉክክር የሚደረግባቸው የስፖርት አይነቶችም እየጨመሩ እንደሚሄዱ አብራርተዋል።

የስፖርት ማህበሩ አርባ ዘጠኝ ዩኒቨርሲቲዎችን በአባልነት አቅፎ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ አባይ፤ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ውድድሮች ሲካሄዱ እንደነበር አስታውሰዋል። በዚህም ብዙ ቱሩፋቶች መገኘታቸውን ገልጸዋል። ይሁን እንጂ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ዩኒቨርሲቲዎች የመማር ማስተማር መርሀ ግብር



**ፌስቲቫሉ የፊታችን ቅዳሜ ከሰዓት በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በሚደረግ የመክፈቻ መርሀ ግብር ይጀመራል፣**

መዛባቱን ተከትሎ ውድድሩን ማካሄድ ሳይቻል እንደቀረ አስረድተዋል።

እንደ አቶ አባይ ገለጻ፣ ሰፊ አላማ ያለው ይህ የውድድር መድረክ በመቋረጡም ብዙዎች ቁጭት አድሮባቸዋል። ያም ሆኖ ትምህርት ሚኒስቴር ዩኒቨርሲቲዎች በተቻለ መጠን ተመሳሳይ የመማር ማስተማር መርሀ ግብር እንዲኖራቸው ማድረጉ ፌስቲቫሉ የሚጀመርበትን እድል ፈጥሯል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ስፖርት በየተቋማቱ እንዲስፋፋ በማድረጉ፣ የትምህርት ተቋማት ከመማር ማስተማር እንዲሁም ከምርምር ሥራዎች ባሻገር በተቻለ መጠን በስፖርት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉ ያለው ፍላጎት ውድድሩ እንዲጀመር ምክንያት ሆኗል። የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲም ማዕከል በመሆኑና ካለው ፍላጎት አንፃር የውድድሩ አስተናጋጅ እንዲሆን መመረጡን አቶ አባይ አክለዋል።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ደረጄ እንግዳ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የስፖርት ማህበሩ ዩኒቨርሲቲው ውድድሩን እንዲያስተናግድ ጥያቄ ሲያቀርብ ለዝግጅት አጭር ጊዜ ቢሆንም በደስታ መቀበሉን ተናግረዋል።

እንደ ፕሬዘዳንቱ ገለጻ፣ ዩኒቨርሲቲው ያሉት ተማሪዎች ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዘ ሥራ የሚሠሩ ቢሆኑም፤ ስፖርት ሁሉንም የትምህርት ዘርፍ የሚያቀናጅ ነው። ስለዚህም የስፖርት ማህበሩ የአስተናጋጅነቱን ጥያቄ ካቀረበ ጊዜ አንስቶ ለውድድሩ አስፈላጊውን ሁሉ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል። የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብዙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ባይኖሩትም በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማና አካባቢው ያሉትን በርካታ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ውድድሩን ለማስተናገድ ይጠቀምባቸዋል።

ዩኒቨርሲቲው ዝግጅቱን አጠናቆ በውድድሩ የሚሳተፉ እንግዶችን ከዛሬ ጀምሮ እንደሚቀበል የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፣ ፌስቲቫሉ «ስፖርት ለአንድነትና ለጋራ እድገት» በሚል መሪ ቃል ይካሄዳል ብለዋል። ይህም በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ተማሪዎች የኢትዮጵያ ልጆች በመሆናቸው ህብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር በጋራና በአንድነት ሠርቶ ለለውጥ መብቃትን ለማመላከት ነው።

በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑትም በየዩኒቨርሲቲዎቹ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ብቻ መሆናቸውን የገለፁት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህም ተቀራራቢ እድሜ ላይ የሚገኙና በተመሳሳይ የትምህርት ሥርዓት የመጡ ያደርጋቸዋል በማለት ተናግረዋል።

የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች አገልግሎት ዲን ሰለሞን ተስፋዬ (ዶ/ር) እንደተናገሩትም፤ ፌስቲቫሉን የተሳካ ለማድረግ አስተናጋጁ ዩኒቨርሲቲ በምግብ፣ መኝታና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች ላይ ዝግጅቱን አጠናቋል።

በኢትዮጵያ ስፖርት እድገት ውስጥ አስተዋፅኦ ከሚያበረክቱ እንቅስቃሴዎች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ውድድር በርካታ ኢሊት ስፖርተኞችን ማፍራቱ ይታወቃል። በተለይም በውሃ ዋና ስፖርት ኢትዮጵያን በኦሊምፒክ ደረጃ መወከል የቻሉ ስፖርተኞችን ያፈራ ሲሆን፤ በእግር ኳስም በፕሪሚየር ሊግ ደረጃ የሚጫወቱ በርካታ ተጫዋቾችን ማፍራት ችሏል። ይሁን እንጂ ለመጨረሻ ጊዜ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከተካሄደ ወዲህ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ተቋርጦ ቆይቷል።


## አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች አቶ አበበ እሸቱ አበራ ወ/ሪት መሰረት አበራ እሸቱ ላይ የመጥፋት ውሣኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል። ስለሆነም ወ/ሪት መሰረት አበራ እሸቱን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ጥር 29 ቀን 2017 ዓ/ም 4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**የካ ምድብ ችሎት**

አመልካች አቶ ልብሰወርቅ አስፋው ሺበሺ ተጠሪ ወ/ሮ ሙሉ ጌታሁን ሞገስ ላይ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል።
ስለሆነም ተጠሪ ካሉ ወይም ያሉበት የሚያውቅ ሰው ካለ በ26/05/2017 ዓ.ም ጠዋት 3፡30 ሰዓት በአ/አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአ/አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት**

በከሣሽ፡- አቶ ግርማቸው አደመ እና በተከሣሾች፡- 1ኛ አቶ ሽመልስ አስፋው 2ኛ. አቶ ሱልጣን አማን መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 5ኛ ፍ/ብሔር እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልስዎን በጽሁፍ ለ22/05/2017 ዓ.ም4፡00 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም አዳሀኖም ብስራት ፋና የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-67740 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር LH172-0028162 ሞዴል KG-LH172V-SRPDS-G የሞተር ቁጥር 5L-4845943 የሊብሬ ቁጥር 098853/048737 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ7/5/2017 ዓ.ም አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራንዮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች ወ/ት የሻረግ አሊ በያን ወ/ሪት ገነት አሊ በያን ላይ የመጥፋት ውሣኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል።
ስለሆነም ወ/ሪት ገነት አሊ በያን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ጥር 29 ቀን 2017 ዓ/ም 4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**የካ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና በተከሳሽ አቶ ቡባ ሱለይማን መሐመድ መካከል ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ ለ25/5/2017 ዓ.ም 3፡40 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 3ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል። በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለእዳ 1. አቶ ተለለኝ አስራቴ 2. መልካሙ ሰንበታ ኢንተርሙ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 6ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሑፍ በ20/5/2017 ዓ.ም 3፡30 ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ኢ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለእዳ አቶ ወንደሰን ደምሴ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሑፍ በ27/5/2017 ዓ.ም 3፡32 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡና ክስ ለመስማት በ6/6/2017 ዓ.ም 4፡00 ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ኢ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ፔቭ ሎጅስቲክስና ንግድ ሥራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በተከሳሽ ትእግስቱ ሐይሉ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አወቀው መልስዎን በጽሑፍ ለ29/5/2017 ዓ.ም 5፡20 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ፡- 1ኛ ስኬት ባንክ አ.ማ እና በተከሳሾች፡-
1. አቶ ታምሩ ማንያዘዋል ግርማ
2. አቶ ኤርምያስ አዲሱ ለማ
3. አቶ ብርሀኑ ገዙ ወ/ጊዮርጊስ
4. ወ/ሮ ሲሳይ አዲሱ ገ/ስላሴ
5. አቶ ቢኒያም ሀ/ሚካኤል ከበደ

መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሾች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ19/05/2017ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ20/05/2017 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢ ችሎት ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት፡- ስኬት ባንክ አ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ፡- 1ኛ ገላኔ እሸቱ 2ኛ ሙና ይመር 3ኛ ጃሌ በከሬ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ21/05/2017ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ22/05/2017 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ**

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት፡- ስኬት ባንክ አ.ማ በተከሳሾች/ተጠሪዎች/ባለዕዳዎች፡- 1ኛ መሰረት ጌታቸው 2ኛ ማናየ ማሞ 3ኛ ደረጀ ተሾመ 4ኛ መስከረም ጌታቸው መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ21/05/2017 በ3፡30 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ22/05/2017 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ**